

በአዋሳ ከ/ማ/ ት/ ቤት ከግቢ መሬቱ ፍሬፍሬዎች



ስለሰበካ ጉባኤ የተደረገ አጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ይህንን ይመስል ነበር



www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ፡፡ »

አዘጋጅ
ልሣነወርቅ በዛብኅ ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ፡፡

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማ ው ጫ

## አርእስት ፤ ገጽ

ደብዳቤዎች ........ ፩
ኅሀ ሲቀድ ........ ፪
ሰዎች ማን ይሉኛል ........ ፬
ሰዎች ማን ይሉኛል ........ ፬
የሚያስደስት ተስፋ ........ ፭
ከሞት ወደ ሕይወት ........ ፮
ተክለ ሃይማኖት ሐዋርያ ........ ፰
መመስከር እንደጊዮርጊስ ........ ፲
ስብከተ ወንጌል ........ ፲፩
ቤተ ክርስቲያን ባለፈው ዓመት ........ ፲፫
የአባ ወልደ ማርያም ቢሆንኝ አጭር የሕይወት ታሪክ ........ ፲፭
የፍጡርን ችግር በፍጡር ........ ፲፮
የግብርና በረከት ........ ፲፯
ቅዱስ ጋብቻ ........ ፲፰
የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ........ ፲፱
ዘመን ካልሠሩበት ........ ፳
ለፍርድ ትቀርባለህና ተዘጋጅ ........ ፳፪

# ደብዳቤዎች

ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ እነሆ እኔ ያሉኝ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ይሆናሉ ፡፡

1ኛ/ በየወሩ እየታተመ የሚወጣው ትንሣኤ መጽሔት ክርስቲያናዊ ሕይወትን እንደሚገነባ እሙን ነው ታዲያ በእናንተ በኩል ዘደፈነ ወርቆ ወርቁን የቀበረ እንደተባለው አይሆንባችሁም ወይ ? ማለትም ተዘጋጀ እንጂ ወደሚፈለግበት አቅጣጫ የሚላክበትን መንገድ አልፈለጋችሁም ፡፡

እስከ አሁን አንዳንድ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ሲያገኙ በርከት ያሉ ክፍሎች ግን ለማግኘት አልቻሉም ይህ ስላልገባኝ ሁኔታው በትንሣኤ መጽሔት ይብራራልኝ ፡፡

2ኛ/ ስለ ዓለም የተፈላሰፉ ፈላስፋዎች ስማቸው በዓለም ታዋቂ ሲሆን በዓለም ልዩ የሆነው ድምጻዊው ቅዱስ ያሬድ እንዳይታወቅ ያደረገው ዋነኛው ችግር ምንድን ነው ? ለወደፊትስ ስለ ዚህ ሊቅ ያለው ዕቅድ የቱን ያህል ነው?

በዕቅዱ ፕሮግራም እኔም በበኩሌ ክርስቲያናዊ ግዴታዬን እንድወጣ እኔን መሰል ጓደኞችንም እንዳበረታታ በመጠኑ እንዲገለጽልኝ እወዳለሁ ፡፡

የቤተ ክርስቲያን አፍቃሪዋና አክባሪዋ ልጃችሁ ዲያቆን ምስጋናው አምባው

ከሲዳሞ ቅ/ ሚካኤል

ዲያቆን ምስጋናው አምባው እንደጠየቅካቸው ያሉ ጥያቄዎች በብዛት ይደርሱናል መልሳቸውንም በየጊዜው እንሰጣለን ነገር ግን ጥያቄዎች ካለመሟላታቸው የተነሣ ተመላልሰው ይጠየቃሉ ፡፡

የመጀመሪያው ጥያቄህ በየወሩ እየታተመ የሚወጣው ትንሣኤ መጽሔት ክርስቲያናዊ ሕይወትን የሚገነባ ሲሆን ለሁሉም ባለመዳረሱ ወርቁን እንደቀበረው ሰው አይሆንባችሁም ወይ ? በማለት የሚላክበትን መንገድ ሳይቀር ጠቁመሃል ፡፡

ጥያቄህ በጣም ጥሩ ነው በየወሩ እየታተመ የሚወጣው ትንሣኤ መጽሔት በቁጥር አነስተኛ ከመሆኑም ሌላ በየሀገረ ስብከቱም በብዛት የማይሰራጭ መሆኑ የማይታበል እሙን ነገር ነው ፡፡

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ሁለት ዓይነት ችግሮች አሉበት አንደኛው የመጽሔቱ እትም ቁጥር ማነስ ሲሆን ሁለተኛው የታተመውን መጽሔት እነሡ በዛም ለዓይነትም ቢሆን ለአህጉረ ስብከቶች በወቅቱ የማድረሱ ሁኔታ ነው ፡፡

በአንደኛ ደረጃ የመጽሔቱን ቁጥር በርከት አድርጐ ለማሳተም የገንዘብ ኃይልን ይጠይቃል የገንዘብ ኃይል ሊገኝ የሚችለው ደግሞ በየአህጉረ ስብከቱ የሰበካ ጉባኤ በሚገባ ተጠናክሮ ክርስቲያኖች የሚፈለግባቸውን አስተዋጽኦ ለቤተ ክርስቲያን መክፈል ሲችሉ ነው፤ ይህ ካልሆነ በአሁኑ ይዞታ መጽሔቱ ለመላው አህጉረ ስብከት ሊደርስ ኀች ላል ብሎ መገመቱ ያስቸግራል ፡፡

ሆኖም አሁን ከሚታተመው መጽሔት ባይበዛም ለጥቂቶቹ አህጉረ ስብከትና በማኅበርተኛነት ለተመዘገቡ ምእመናን እንልካለን በሌላ በኩል ደግሞ በየሀገረ ስብከቶች ርእሰ ከተማ የሚሠሩ የቤተ ክህነት ባለሥልጣኖች ከስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልእኮ መምሪያ ሐላፊ ጋር ግንኙነት ቢያደርጉ ባይበዛም በመጠኑ ጥቂት ጥቂት መጽሔቶች ሊደርሷቸው ይችሉ ነበር ፡፡ ነገር ግን እስከ አሁን ድረስ ከአሕጉረ ስብከት ባለሥልጣኖች የሚበልጡት መጽሔቶችንም ሆነ ጋዜጦችን ለመውሰድ በማኅበርተኛነት ተመዝግበው ገንዘብ ስላልከፈሉ አይላክላቸውም ፡፡

ዲያቆን ምስጋናው እንደጠቀስከው የሰንበት ት/ቤቶች ወጣቶችም ቢሆኑ አንተ እንደምትለው ታዋቂ ሰው ያላቸው ብቻ ሳይሆኑ የመጽሔቱን ዋጋ ለከፈሉ ሁሉ መጽሔቱ በየወሩ ይላክላቸዋል ዋጋው ከተከፈለ ባላላኩ በኩል የሚደርሰው ችግር ቀላል ነው ችግሩ ዋጋውን በቅድሚያ አለመክፈሉ ብቻ ነው ፡፡

ዲያቆን ምስጋናው "ላለፈው ክረምት ቤት አይሠራም" እንደሚባለው ያለፈውን ተወውና ለወደፊቱ መጽሔቱ በየወሩ እንዲደርስህ ከፈለግህ የዓመቱን ሂሳብ ከእነመላኪያው ለመጽሔት ብር 13.80 (አሥራ ሦስት ብር ከሰማንያ ሳንቲም) ከፈልና የመጽሔታችን ደንበኛ ሁን ሌላም በዚሁ መሠረት ደንበኛ ለመሆን የሚፈልግ ካለ እንቀበላለን ፡፡

በሁለተኛው ጥያቄህ ቅዱስ ያሬድን በዓለም እንዳይታወቅ ያደረገው ምንድን ነው ? ብለሃል ቅዱስ ያሬድ በዓለም አይታወቅም ለማለት አይቻልም ቱሪስቶች ከአውሮፓ ፤ ከእስያ ፤ ከአሜሪካ ፤ ከመሳሰሉትም ክፍለ ዓለማት በየዓመቱ በወርኃ ጥር የሚመጡት በጥምቀተ በዓል የሚዘመረውን የያሬድን ዝማሬ ለመስማትና የካህናቱንም ሽብሸቦ በፎቶግራፍ አንስተው ድምጻቸውን ቀርጸው የሙዚቃውንም ደራሲ ጠይቀው ታሪኩን ጽፈው ለመሄድ ነው ስለዚህ ቅዱስ ያሬድ በዓለም አልታወቀም ከማለት ይልቅ እኛ በቂ የሆነ መታሰቢያ ትምህርት ቤት አላቋቋምንለትም ማለቱ የተሻለ ይመስለናል ፡፡

በጥያቄህ መደምደሚያ ላይ ስለ ቅዱስ ያሬድ የታቀደ ካለ እኔና እኔን የመሰሉ ጓደኞቼ በዕቅዱ ላይ ለመሳተፍ እንድንችል ግለጹልን ብለህ ጠይቀሃል

እጅግ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው በቅዱስ ያሬድ ስም በአዲስ አበባ ከተማ ቤተ ክርስቲያን እየታነፀ ነው ከቤተ ክርስቲያኑም ጋር ፀዋትወ ዜማ የሚስፋፋበት ትምህርት ቤት እንዲሠራ ፕላኑ ወጥቶ አልቆ የሚሠራበት ገንዘብ የሚገኝበት መንገድ እየተፈለገ ነው ፡፡

አንተና መሰሎች ጓደኞችህም ክርስቲያናዊ ግዴታችሁን ለመወጣት እንድትችሉ ለዚሁ ለተጀመረው ቤተ ክርስቲያን ማስፈጸሚያና ለታቀደው ትምህርት ቤትም መሥሪያ የሚሆን የተቻላችሁን ገንዘብ አስተዋፅዖ ማድረግ ነው ፡፡

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

ርእሰ አንቀጽ

# ጎህ ሲቀድ

የጨለማው ክፍለ ጊዜ ወደማለቁ ተቃርቦ የብርሃኑ ክፍለ ጊዜ ሲቃረብ ጎህ ቀደደ ይባላል ይህም ፍጹም ጨለማ ያልሆነ ብርሃኑም በደንብ ያልጐላ እንደማለት ነው ፤ ከጎህ ቀጥሎ የሚተካው የፀሐይ ብርሃን ነው በዚያን ጊዜ ጨለማው ሙሉ በሙሉ ተወግዶ ብርሃን ይሆናል ።

የሰው ልጆች ለሥራ ይንቀሳቀሳሉ ይወጣሉ ይወርዳሉ ፣ ገበሬዎች ያርሳሉ ይቆፍራሉ ነጋዴዎች ይነግዳሉ ሌሎችም የተመደቡበትን ሥራ ያከናውናሉ ፣ ይህንንም ስንል የጨለማው ጊዜ ለሰው ልጆች ጥቅምን አያበረክትም ማለት አይደለም ።

ለምሳሌ ሰዎች በቀን ሥራቸውን ሲያከናውኑ ውለው ሌሊት ደግሞ ቀን በሥራ የደከመውን ሰውነታቸውን በዕረፍት ያድሳሉ ፤ ሌሊት በእንቅልፍ የታደሰ ሰውነታቸውም በቀን ተገቢውን ሥራ ለመሥራት በቂ ኃይልን ለማግኘት ይችላል ።

መዓልትና ሌሊት በሚያደርጉት ለውጥ የሰው ልጆች ለሚሠሩት ሥራ ሁሉ ኃይልንና ቅልጥፍናን እያገኙ ሕይወታቸውን ያለ ድካምና ያለ ብስጭት በደስታ ለመምራት ይችላሉ ።

በሰዎች ዘንድ ዘመነ ክረምት እንደጨለማ ዘመነ ሐጋይ እንደ ብርሃን ይቆጠራል ከዚህ የተነሣ በቦታ ተራርቀው የሚገኙ ወገኖች ክረምቱ ሊጀምር ሲል ተገናኝተው ሲለያዩ ፀሐይ ሲወጣ መስከረም ሲነጋ በሰላም እግዚአብሔር ያገናኘን በማለት ሰላምታ ይለዋወጣሉ ።

ክረምቱን እንደ ጨለማ የሚያስቆጥሩት የዝናሙ ክብደት ፣የጉሙና ጭጋጉ አፈና ፣ ጐርፉና ጭቃው ፣ ዳጡና የአየሩ ቅዝቃዜ ፣ የውሀው ሙላትና የመሳሰሉትም ናቸው የተጠቀሱት ሁሉ በሩቅ ካለ ዘመድ ጋር ለማገናኘት ስለማያስችሉ ክረምትን እንደ ሌሊት አስቆጥረውታል ።

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዘመነ ክረምትን ከባድነት ሲገልጽ ሽሽታችሁ በክረምት እንዳይሆን ጸልዩ ብሏል ማቴ ፳፬. ፳ ።

ቅዱስ ያሬድም በበኩሉ ከነሐሴ ፳፭ - ዮሐንስ ያለውን ቀን ጎህ ጽባሕ የንጋት ጎህ ብሎ ሰይሞታል ክረምቱ ወደማለቁ ተቃረበ ሲል ነው ።

አሁንም የክረምቱ ወራት ተገባዶ የበጋው ጭላንጭል እየታየ ነው ከክረምቱ ሁለቱ እጅ አልፎ አንድ እጁ ብቻ ቀርቷል ከጥቂት ጊዜ በኋላ አዲሱ ዘመን መጋቢነቱን ይጀምራልዘመነ ሉቃስ መግቦቱን ጨርሶለሚቀጥለው ዘመነ ዮሐንስ ሊያስረክብ የሰው ልጆች ባለፈው ዘመን የሠሩትን ሥራ በዐይነ ልቡና አተኩረው የመመልከት ግዴታ አለባቸው ።

ሥራ ካልሠሩት በዓይን በመመልከትና በምኞት ብቻ ሊከናወን አይችልም የሥራ ፍሬ የሚሰበሰበው ከመሥራት ነውና ሥራ የማይሠራ ሰነፍ ሰው ዘመኑ ሲለወጥ በመመልከቱና ከጊዜው በመድረሱ ብቻ ደስታን ሊጐናጸፍ አይችልም በዘመነ ሉቃስ ጠንክሮ የሠራ አሁን ሲደሰት ያልሠራ ደግሞ በስንፍናው ያዝናል ይተክዛል ፣ ያለፈው ዘመን ለአንዳንዶች ሰዎች የሥራ የጤና የብልጽግና ፣ የፍቅር ፣ የሰላም የኅብረት ጊዜ ሆኖላቸው አልፎአል ለአንዳንዶች ሰዎች የችግር የብስጭት የመከራ ወዘተ ሆኖባቸው ይሆናል ። ነገር ግን ደስታም ሆነ መከራ ብልጽግናም ሆነ ድኅነት በአንድ ሰው ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም ፤ ያዘነው ይደሰታል ፣ የተደሰተው ያዝናል ፤ የተረጋጋው ይበሳጫል ፣ የተበሳጨው ይረጋጋል ፤ የበለጸገው ይደኸያል ፤ የደኸየው ይበለጽጋል ፤

ስለዚህ የሰው ልጅ የተስፋ ባለቤት ስለሆነ ተስፋ ሳይቆርጥ ችግሩንና ኃዘኑን ያስወግድለት ዘንድ እየሠራ እግዚአብሔርን መለመን አለበት ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለምና ።

ተስፋ አያሳፍርም ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ እንደተናገረው ባለፈው ዘመን አልተደሰትኩምና ምንም ቢሆን ችግር ከራሴ አይወጣም ስንፍናም ከእኔ አይወገድም በማለት ተስፋ ቢስ ሆኖ መቀመጥ የሰው ልጆች ዓላማ አይደለም ውሃ ሁልጊዜ እንደጠራ አይኖርም በክረምት ዝናም ዘንቦ ጐርፍ ስለሚጨመርበት ይደፈርሳል በበጋ ደግሞ ይጠራል እንደዚሁም የሰው ልጅ ሁልጊዜ አይደሰትም ዘወትር እንዳዘነም አይኖርም ለመከራም ለደስታም የተዘጋጀ በመሆኑ ያዝናል እንዲሁም መልሶ ይደሰታል ።



ስለዚህ እያንዳንዱ ሰው ከሁሉ አስቀድሞ ተፈጥሮውን የማወቅ ግዴታ አለበት ተፈጥሮውን በሚገባ ከተረዳ ባለፈው ዘመን ሳይሠራ በስንፍና ኑሮ እንደሆነ ለሚቀጥለው ዓመት ጠንክሮ ለመሥራት ይዘጋጃል ባለፈው ዓመት አጥቶ ተቸግሮ ታሞ አዝኖ እንደሆነ በሚቀጥለው ዘመን ችግሩ ሁሉ ተወግዶለት እንደሚደሰት ተስፋ ያደርጋል ።

ባለፈው ዘመን ሕገ እግዚአብሔርን በማፍረስ ተንኮል ሠርቶ ከእግዚአብሔር ርቆ እንደሆነ ለሚቀጥለው ዘመን ንስሐ ገብቶ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቆ መልካም ሥራ ለመሥራት ይጥራል በጠቅላላው የሰው ልጆች ዓላማ እንደዚሁ መሆን ይገባዋል ።

ጎህ ሲቀድ ከመኝታው ተነሥቶ ለቀን ሥራው የማይዘጋጅ ሰው በሽተኛ እንጂ ጤነኛ ሊባል እንደማይችል ዘመንም አልፎ ዘመን ሲተካ ለአዲስ ሥራ ታጥቆ የማይነሣ ሰው ጤነኛ ሊባል አይገባውም ስለዚህ ዘመን አልፎ ዘመን ለመተካት ጎህ ሲቀድ እያንዳንዱ ሰው ካለፈው ዘመን የበለጠ ሥራ ለመሥራት መዘጋጀት ይገባዋል ።

# ለንባብ ጀማሪዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ

“የሉቃስ ወንጌል ምዕ. ፩ ፣ ፴፱ - ፶፯

ማርያምም በዚያ ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ወጣች ወደዘካርያስም ቤት ገብታ ኤልሳቤጥን ሰላም አለቻት ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማህፀንዋ ውስጥ ዘለለ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች ።

አንች ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ነሽ የማኅፀንሽ ፍሬም የተባረከ ነው የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆናል ? እነሆ የሰላምታሽ ድምፅ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማኅፀኔ በደስታ ዘልሏልና ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፁዕት ናት ።

ማርያምም እንዲህ አለች ነፍሴ ጌታን ታከብረዋለች መንፈሴም በአምላኬ በመድኃኒቴ ሐሤትን ታደርጋለች የባሪያይቱን ውርደት ተመልክቷልና እነሆ ከዛሬ ጀምሮ ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል ብርቱ የሆነ እርሱ በእኔ ታላቅ ሥራ አድርጓልና ስሙም ቅዱስ ነው ምሕረቱም ለሚፈሩት እስከ ትውልድና ትውልድ ይኖራል ።

በክንዱ ኃይልን አድርጓል ትዕቢተኞችን በልባቸው አሳብ በትኖአል ገዥዎችን ከዙፋናቸው አዋርዶአል ትሑታንንም ከፍ አድርጓል የተራቡትንም በበጎ ነገር አጥግቧል ባለ ጠጎችንም ባዶአቸውን ሰዶአቸዋል ለአባቶቻችን እንደተነገረ ለአብርሃምና ለዘሩ ለዘለዓለም ምሕረቱ ትዝ እያለው እስራኤልን ብላቴናውን ረድቷል ።

ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል በእርሷ ዘንድ ተቀመጠች ወደ ቤቷም ተመለሰች ።



www.ethiopianorthodox.org

# "ሰዎች ማን ይሉኛል"

በማንኛውም ማኅበረ ሰብእ ውስጥ አባል ሁኖ መኖር የሚቻለው "ሰዎች ማን ይሉኛል?" በማለት ራስን መጠየቅና የራስን ማንነት ወይም ምንነት በሚገባ ማወቅና ለሌላውም ማሳወቅ ማኅበራዊ ግዴታ ነው ። ይህማ ካልሆነ ራስን ሳያውቁ ሌላውን ማወቅ ስለማይቻል ኃጥኡን ጻድቅ ፣ ጻድቁንም ኃጥእ ፣ እንደማድረግ ይቆጠራል ።

እያንዳንዱ ግለሰብእ ወይም ማኅበረ ሰብእ በስተጀርባው ያለውን ስሙን ካላወቀ ሲረግም ውሎ የመረቀ ፣ ሲያጭድና ሲመነጥር ውሎ የዘራና የተከለ ፣ ሲበትን ውሎ የሰበሰበ ይመስለዋል ።" "ሰዎች ምን ይሉኛል? ብሎ የሚያስብና ጠይቆም የሚረዳ ከሆነ ግን ማንም ቢሆን ከስሕተቱ ይታረማል ፤ መልካምም ገዞ የሚጓዝ ከሆነ መልካም ሥራውን በበለጠ ያስፋፋል ፣ መልካም ሠርቶ የመመስገንና መልካምን ስም የማግኘት ጉጉቱም እየበረታ ይኼዳል ፣ በሚሠራው ሥራ ውጤት ደስተኛ ከመሆኑም በላይ በኅብረተሰብኡ ዘንድ ተወዳጅነትንና ምስጉንነትን ያተርፋል በመልካም ሥራውም ምሳሌ ለመሆን ይበቃል ።

በሀገራችን በየመዓዘኑ የሐሳብ መስጫ ሣጥኖች የሚንጠለጠሉትም የዚህን ጥያቄ መልስ ለማግኘት ነው ።

በመሠረቱ ይህን ጥያቄ የጠየቀው ራሱ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ፣ ማንን ነበር የጠየቀው ? ለምንስ ጠየቀ ? እነዚህ ጥያቄዎች የሁላችንም ሊሆኑ ይቻላሉ ፣ እንግዲያው መልሶቹን በሚቀጥለው መስመር መመልከት ይጠቅማል ።

ታሪኩ እነሆ ፣

ጌታችን መድኀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደቀ መዛሙርቱ ጋር በፊሊጶስ ቂሳርያ አውራጃ ወደሚገኙት መንደሮች በገባ ጊዜ "ሰዎች ማን ይሉኛል" ሲል ደቀመዛሙርቱን ጠየቃቸው ። እነርሱም መጥምቁ ዮሐንስ ነው ይሉሃል ፤ ሌሎችም ኤልያስ ነው ይሉሃል ፤ አንዳንዶቹም ኤርምያስ ነው ይሉሃል ፤ ሌሎች ደግሞ ከቀደሙት ታላላቅ ነቢያት አንዱ ነው ይሉሃል አሉት ።

እንግዲህ ከዚህ መልስ እንደምንረዳው በዚያን ጊዜ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት በሰዎች ዘንድ ገና ያልተገለጸ ቢሆንም ኅብረተሰብኡ እንደ አንድ ታላቅ ነቢይ የሚመለከተው መሆኑን ነው ። ታዲያ መልሱ ትክክል አልነበረም በዚህም ምክንያት ጌታ መልሶ መጠየቅ ነበረበትና "እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ" በማለት እንደገና ጠየቃቸው ፤ ከደቀ መዛሙርቱ አንዱ ጴጥሮስ መለሰና "አንተ በእውነት የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ነህ አለው ። አርኪ መልስ ነበር ፤ ትክክለኛ መልስ ሲገኝ በጣም ደስ ያሰኛል ። በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ጴጥሮስ ትክክለኛውን መልስ ሰጠው ለከፍተኛ ሥልጣንም በቃ የገለጸልህ ሥጋዊ አባት ሳይሆን ሰማያዊ አባት ነውና አንተ የተመሰገንህ ነህ አንተ አለት ነህና በዚህች አለት ላይ ቤተ ክርስቲያኔን አሠራለሁ ። የሲኦል ደጆች ቢያናውጡአት አይችሉም ፤ የመንግሥተ ሰማያትን መክፈቻ እሰጥሃለሁ ፤ በምድር ያሠርኸው በሰማያት የታሠረ ይሆናል ፤ በምድር የፈታኸው በሰማያት የተፈታ ይሆናል ። የሚል ሥልጣን ተሰጠው ።

ጌታ ኢየሱስ ማንነቱን ካልተረዱ በሚገባ ማስረዳት ዋና ዓላማው ስለሆነ ትክክለኛ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለመግለጽ ፈቅዶ በስድስተኛው ቀን ሙታንንና ሕያዋንን የሚገዛ ሥልጣን ያለው አምላክ ስለሆነ ፤

ሀ/ ከሚከተሉትና በሕይወት ከነበሩት ደቀ መዛሙርቱ መካከል ሦስቱን ማለትም ጴጥሮስን ፣ ዮሐንስንና ወንድሙን ያዕቆብን አስከትሎ ደብረ ታቦር ተብሎ ወደሚጠራው ታላቅ ተራራ ወጣ ፤

ለ/ ነቢዩን ሙሴን ሙቶ ከተቀበረ ከ፲፯፻፰ ዓመታት በኋላ (በ፫ሺ ፭፻፹፫ ዓ.ም.) ከመቃብር ዓለም አስነሣው ፣

ሐ/ ከምድራውያን ዓለም የራቀውንና የተሠወረውን በአፍራሰ እሳት በሠረገላ እሳት ያረገውን ኤልያስን ከ፱፻ ዓመታት በኋላ በአምላክነቱ ሥልጣን አመጣና አምላክነቱን አስመሰከረ ፤

ይኸውም ፣

፩. በደቀ መዛሙርቱ ፊት መልኩ ተለወጠ ፣

፪. ፊቱ እንደ ፀሐይ አበራ

፫. ልብሱ እንደበረዶ ነጣ

፬. ነቢያት ሙሴና ኤልያስ ከእሱ ጋር ሲነጋገሩ ተሰሙ በዚህ ጊዜ ጴጥሮስ "አቤቱ ጌታ ሆይ ብትፈቅድስ አንድ ላንተ ፣ አንድ ለሙሴና አንድ ለኤልያስ ሦስት ቤቶች እንሥራና ከዚህ እንኑር በማለት ያለውን ምኞት ገለጸ ።

፭. ይህን በሚነጋገርበት ጊዜ እነሆ ብሩህ ደመና መጣና ጋረዳቸው ፤ ከደመናውም ውስጥ "ይህ የምወደው ልጄ ነውና ስሙት የሚል ድምፅ ተሰማ ፤ ደቀ መዛሙርቱም ይህን ቃል ሲሰሙ ፈሩ ደነገጡም ፤ በፊታቸውም ተደፍተው ከምድር ላይ ወደቁ ፤ ጌታ ኢየሱስም ቀርቦ ዳሰሳቸው ፤ አይዟችሁ አትፍሩ ፣ ተነሡ" አላቸውና ተነሡ ነገር ግን ከጌታ ከኢየሱስ በቀር ማንንም አላዩም ።

ከዚያም ከተራራው ሲወርዱ ያዩትንና የሰሙትን ለማንም እንዳይናገሩ አስጠነቀቃቸው ። ምሥጢርን መጠበቅ ይገባልና ።

እንግዲህ "ሰዎች ማን ይሉኛል?" በሚል መነሻ ተነሥተን የተከታተልነው ትምህርት ምን ዓይነት ትምህርት ይሰጠናል ? ብለን ብናስብ እንደሚከተለው ሆኖ እናገኘዋለን ። ይኸውም ሰዎች ማን ምን ይሉኛል ብሎ ራስን መጠየቅና መልሱን እንደየሁኔታው ማግኘት ብልህነት ነው ። ወዳጅንና መሰልን ጠይቆ መረዳትም ያኮራል ። እንጂ አያሳፍርም ።

በዚህም መሠረት መልካም ሠርቶ በሥራ መግለጽ ተገቢነቱን እናያለን ። ይህም ከግል ቤት መጀመር ይኖርበታል ማንኛውም ተግባር ማደግ ያለበት ጥቂት በጥቂት ነውና ። ሚስት አግብቶ የሚኖር ወንድ ፣ ወይም ባል አግብታ የምትኖር ሴት ሚስቱ ምን ትለኛለች? ወይም ባሌ ምን ይለኛል? ወይም በጠቅላላ ቤተሰዎቼ ምን ይሉኛል? ቤተሰዎቼንና ራሴን በትክክል መምራት ችዬ ይሆን ? ብሎ ማሰብና የራስን ጉድለት ማስተካከል ይኖርበታል ።

ወደ ጐረቤትም ወጣ ብሎ ማን ትሉኛላችሁ ? ወይም ምን ትሉኛላችሁ? ብሎ መጠየቅ ያስከብራል እንጂ አያዋርድም ፣ ጐረቤት ሊያገኝ የሚገባውን መብቱን ከሰጠ ሊነቅፍ ሊያዋርድ አይችልም ፣ እንዲያውም ይመርቃልም ያመሰግናልም እንጂ ፣ ስሕተት (ጉድለት) ካለ ሊታረም የሚገባውን ነገር ከመናገር አይመለስም እቅጩን ይናገራል ፣ ሊያጋንንም ይችላል ፣ ታዲያ በዚያን ጊዜ ማኩረፍ ሳይሆን ጉድለትን ማስተካከል፣ ስሕተትን ማረም ግዴታ እንደሆነ ከላይ የተጠቀሰው ቃል ያስገነዝባል ። ክፉ ሠርቶ ከመነቀፍ መልካም ሠርቶ መመስገን ይመረጣል ።

ከዚህም ተነሥቶ እድገቱን በማሳየት ሃይማኖታውያንን የሚመሩ የሃይማኖት መሪዎች ዓለማውያንን የሚመሩ የዓለም መሪዎች ሊመሩበት የሚቻል መመሪያ ይሆናል ፤ በእውነት ቢመሩበትም ይጠቅማቸዋል ። የእነሱን አመራርና የሚመሩት ሕዝብ ኑሮ ሁኔታን ማጥናት ያስችላቸዋልና ።

የተከታያቸውን ሕዝብ ልብ ትርታ እንዲያዳምጡና ፍላጐቱን ለማሟላት ጥረት እንዲያደርጉ ይገፋፉቸዋል ። ፍላጐቱን ካሟሉም መልካም ማስመዝገብ ያስችላቸዋልና ።

ስለዚህ ከአንድ ግለሰብእ ቤት ጀምሮ እስከ መጨረሻዎቹ የዓለም መሪዎች ድረስ ያለው ሁሉ ሊጠቀምበት የሚገባ ቃል ነው ።

መ. ሀብተ ማርያም ተድላ

# የሚያስደስት ተስፋ

ብዙ ቀናት የተጓዙለት መንገድ ተፈጽሞ ከአሰቡት ቦታ ሲደረስ ለተጓዡ የሚሰማው ደስታ የቱን ያህል እንደሆነ እያንዳንዱ ሰው ያውቀዋል ።

አንዳንድ ሰዎች ከፍ ያለ ደስታ ሲሰማቸው ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ደንግጠው ይታመማሉ ፣ አንዳንዶቹ ደግሞ ያለቅሳሉ ይወድቃሉ ፣ ይነሣሉ የሚይዙትና የሚጨብጡትም አጥተው ይርበተበታሉ ።

በዚህ ዓመት በግንቦት ወር ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ቅዱስ ሲኖዶስ ካስተላለፋቸው ዓበይት ውሳኔዎችም አንደኛው የቤተ ክህነት ሠራተኞችን በደስታ ሞልቷቸዋል ፣ ሠራተኞች የተሰማቸውን ደስታ ለመገመት የሚያስችለውም በቢሮም በግቢም በውስጥም የሚወራው ታላቅ ቁም ነገር ቅዱስ ሲኖዶስ ስላስተላለፈው የሠራተኞች የጡረታ መብት መከበር በመሆኑ ነው ።

ቅዱስ ሲኖዶስ በአንድ ዓመት ውስጥ ሁለት ጊዜያት በመሰብሰብ የሚያስተላልፋቸው መንፈሳውያን ውሳኔዎች በርከት ያሉ ቢሆኑም የሠራተኞች የጡረታ መብት ባለመከበሩ ሠራተኞቹን ከፍ ያለ ቅሬታ ይሰማቸው ነበር የዘንድሮው ግንቦት ቅዱስ ሲኖዶስ ግን የሠራተኞችን ችግር ተመልክቶ የጡረታ መብታቸው እንዲከበር በማድረጉ በሠራተኞች ዘንድ ከፍ ያለ መንፈሳዊ ፍቅርን አሳድሮባቸዋል ።

ወሩም ቢሆን የደስታ ወር ተብሎ በሠራተኞች ቃል ሊሠየም የሚገባው ነው ፤ ለብዙ ጊዜ ሲጠበቅ የነበረው ተስፋ ተፈጽሞበታልና ።

ጠቢቡ ሰሎሞን "ለሁሉም ዘመን አለው በሰማይ በታችም ለሆነ ነገርሁሉ ጊዜ አለው ለመትከል ጊዜ አለው ፣ የተተከለውንም ለመንቀል ጊዜ አለው " ብሎ እንደተናገረው ቅዱስ ሲኖዶስ የሠራተኞችን ችግር ተመልክቶ ፣ወቅቱን ጠብቆ ያስተላለፈው ውሳኔ ለሠራተኞች ያጐናጸፋቸው ተስፋ የሚያስደስትና የሚያቀናጣ ነው ለማለት ያስደፍራል ፣

የቅዱስ ሲኖዶስ የስብሰባ ወቅት በደረሰ ቁጥር የሠራተኞች አሳብ የሚያርፈው ስለ ጡረታ መብት የሚተላለፍ ውሳኔ ይኖር ይሆን ? በማለት ነበር ።

የጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጆችም በተለወጡ ጊዜ የሠራተኞች ጥያቄም ሆነ አቤቱታ የሚያተኩረው ስለ ጡረታ መብት አለመከበር ነበር ።መጽሔቶችም ሆኑ ጋዜጦች ለቤተ ክህነት ሠራተኞች የጡረታ መብት እንዲኖራቸው በማለት ያላቀረቡት ጥያቄ በዓምዳቸውም ላይ ያላሰፈሩት ቃል አልነበራቸውም ። ግን ቃላቸው ተሰምቶ ጉዳዩ ከፍጻሜ ሳይደርስ እስከ አሁን ቆይቷል።

የዚህ ዓመት ቅዱስ ሲኖዶስ በወርኃ ግንቦት ተሰብስቦ የቤተ ክህነት ቋሚዎች ሠራተኞች የጡረታ መብት እንዲጠበቅ መወሰኑ እጅግ በጣም ያስመሰግነዋል ።

ከአሁን ቀደም ሠራተኞቹ በሥራ ላይ ሳሉ ሲያገኙት ከነበረው ደመወዛቸው እየተቀነሰ ሲጠቀሙ ቆይተው በዕርጅና (በበሽታ) ምክንያት መሥራት ሲሳናቸው በአገልግሎት በደመወዝ በሞያ አንጻር ሳይሆን በግምት ይኸ ይበቃችኋል ተብለው ይሸነገሉ ነበር።እንጂ በደንቡ መሠረት አገልግሎታቸው ታስቦ ገንዘብ አይከፈላቸውም ነበር ።

ያውም የሚሆነው በሕይወተ ሥጋ የቆዩ እንደሆነ ነው ከሞቱ በኋላ ግን ያው እነሡም አደገም የሚከፈላቸው ገንዘብ ለቤተሰብ አይሰጥም ገንዘቡ ከራሳቸው ሕይወት ጋር ያከትማል ።

እንደዚህ ያለው ተግባር ለሠተራኞች እጅግ በጣም አሳዛኝና ተስፋ የሚያስቆርጥ ሞራልንም ዝቅ የሚያደርግ በመሆኑ የጠቅላይ ቤተ ክህነት አስተዳደር ክፍል ጉዳዩን አጥንቶ ለቅዱስ ሲኖዶስ ስላቀረበ ቅዱስ ሲኖዶስም የቀረበለትን ጥናታዊ መግለጫ ተመልክቶ እንደማንኛውም መንግሥታዊ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች የሠራተኞች የጡረ


www.ethiopianorthodox.org

ታ መብታቸው እንዲከበር ወስኗል ው ሳኔውም“ ሌላ ባል ላላገባች ሚስት ከ ፲፰ ዓመት በታች ለሚገኙ ልጆች”እን ዲተላለፍ የሚል ሲሆን ይኸውም ውሳ ኔ ከግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፫ ዓ.ም.ጀም ሮ በሥራ ላይ እንዲውል አዝዟል ።

ይህ የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔ ማንኛው ንም ሠራተኛ የሚያስደስት ነው ያዕቆ ብ በልጁ ዮሴፍ መጥፋት አዝኖ አርጅ ቶ ደክሞ ዓይኑ ፈዞ ጉልበቱ ደንግዞ ሳለ ልጅህ ዮሴፍ በሕይወት አለ ብለው በነ ገሩት ጊዜ ከድካሙ ተጽናንቶ ከመ ኝታው ተነሥቶ እንደተቀመጠ በዚ ህም የጡረታ መብት መከበር ዜና በሥ ራ የደከሙ ሠራተኞች ሁሉ ሊጽናኑ ሊ በረቱ ይገባቸዋል ። ተስፋ በመቁረጥ ታውረው የነበሩ ሁሉ ዓይኑ ልቡናቸው በተስፋ በርቶላቸው ሥራቸውን በደስ ታ እንደሚያከናውኑ አንጠራጠርም ሊቀ ግዕምራን አባባው ይግዛው የጠ ቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ና የቅርብ ረዳቶቻቸው በቅዱስ ሲኖዶስ በኩል ተቀባይነት እንዲኖረው አድርገ ው በማቅረባቸው ሊመሰገኑ ይገባል ፣

ቅዱስ ሲኖዶስም የሠራተኛውን ች ግርና ፍላጐት ተመልክቶ የቀረበለትን ጉዳይ ያለምንም ቅሬታ በውሳኔ አጽድ ቆ እንዲሠራበት በማድረጉ ከቤተ ክር ስቲያን ጉዳዮች ታላቁን ችግር እንዳስ ወገደ ያስቆጥረዋል ፣ በዚህ ውሳኔ ሠራ ተኛው ሁሉ የሚያቀናጣ ተስፋን ጨብ ጧል እንግዲህ ሠራተኛው መብቱ ስለ ተጠበቀ እንደ አቅሙ ጠንክሮ በመሥ ራት ቤተ ክርስቲያንን የማገልገል ግ ዴታ አለበት ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

# ከሞት ወደ ሕይወት

ክርስቶስን በማመን ፀንቶ ለሚኖር ዘርአ አዳም ሁሉ የቃል ኪዳን እናት እንድትሆን የተመረጠች እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም የነበራትን ታሪካዊ የትሕትና ሥነ ባሕርይና እንዲ ሁም በዚሁ ትሕትና ያገኘችውን ልዕ ልና በሥዕላዊ ንግግር መግለጥ የፈለጉ አንድ ኢትዮጵያዊ ስመ ጥር ባለቅኔ እንዲህ አሉ ።

አዝርዕተ ምድርነ
ያጸንኑ ታሕተ ሶበ ፈረዩ
ፍሬ ይስሕብ አኮኑ መንገለ ታሕቱ አዝ ርዕተ
ወዘከመ እሉ እጐልቁ እሰፍንተ ?
አሐቲሰ ዕፅ ከመ ታግብእ መሬተ
ወከመ ያዕርጋ ሰማያተ
ዕፅ ስሐበት ታሕተ ታሕተ
ወፍሬሃ ሰሐባ መልዕልተ”

ትርጉሙ ፦ “በምድራችን የሚበቅሉ አዝርዕትና አትክልት ሁሉ በሚያፈሩ በት ጊዜ ወደመሬት ማዘንበል ይጀም ራሉ ፣ ይህም የሚሆንበት ምክንያት የፍሬያቸው ክብደት ተክሎችን ወደ ታች ስለሚስብ ነው ። ለዚህም ብዙ ማስ ረጃ አለኝና ስንቱን ልቆጥረው እችላ ለሁ ታዲያ አንዲት ተክል በዚሁ ልማድ መሠረት ፍሬዋን ወደመሬት ለማድረስ ከላይ ወደታች ሳበችው ፍሬዋ ግን ወደ ታች በመጫን ፈንታ ወደላይ በመሳብ ከፍ ከፍ አደረጋት” እንደማለት ነው ።

እንግዲህ እዚህ ላይ “አንዲት ዕፅ” ተብላ የተሠየመች እመቤታችን ቅ/ ማርያም ስትሆን ፍሬ ተብሎ የተጠቀ ሰውም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑ ግልጥ ነው (ሉቃ ፩፡፵፱)

ባለቅኔው በዚህ ሥዕላዊ የንግግር ጥበብና ፈሊጥ ማስተማር የፈለጉት ፍሬ ነገር አለ ። ይኸውም “ወበከመ ፍሉጥ ፍኖተ መሥገርት ወዓሣ ለከዊነ ዓመት ተሐሥሦ ወከዊነ እግዝእት የሐሥሣ ።

“የመረብና የዓሣ መንገድ የተለያየ እንደሆነ እርስዋ ስለትሕትና ገረድ ሆና ማገልገልን ስትመኝ እርስዋን ግን እመ ቤትነት ይጠብቃት ነበር” ሲሉ ሌላው ባለቅኔ ስለእመቤታችን የተነገረውን ምሥጢር እንደመነፅር አጉልተው ለማ ሳየት ፈልገዋል ።

ይህም ቅኔ የተዋቀረበት ታሪካዊ ፍሬ ነገር “እመቤታችን ቅ/ድ/ ማርያም ከነ በሩዋት የታላቅ ሰውነት ሥነ ባሕርያት አንዱ ቅዱሳት መጻሕፍትን የማንበብ ልምድ ነበር ስለዚህም ከዕለታት አንድ ቀን መጽሐፈ ኢሳይያስ ገልጣ ስታነብ “እነሆ ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድን ግልና ትወልዳለች ስሙንም አማኑኤል ትለዋለች” የሚለውን ቃል ተመልክታ ተደነቀች ። በዚህ ጊዜ ታዲያ “ምነው እኔ በሆንኩ” የሚያሠኝ ተምኔታዊ ትም ክህት አላደረባትም ፣ ይልቁንም በትሕ ትና አነጋገር “ይህች አይነትዋ ቅ/ ድን ግል በምትነሣበት ዘመን ደርሼ ምነው ገረድ ሆኜ ባገለገልሁአት ስትል አገል ጋይነትን ተመኘች ። ይህንም ቃል በማ ሰላሰል ላይ ሣለች ቅ/ ገብርኤል ተገል ጦላት ለዚህ እመቤትነት የተመረጠች እርሱዋው ራስዋ መሆኑዋን አስረድቶ ቃለ አብ ክርስቶስን በድንግልና ፀንሳ በድንግልና እንደምትወልድ አበሠራት” ሲሉ መተርጉማን በሚያቀርቡት ትንታኔ ላይ ነው ።

ይህንም ብሥራት ከሰማች በኋላ አክስትዋ ኤልሣቤጥም በስተርጅና የመ ጸነስዋ ምሥጢር ተነግሮአት ስለነበር ይህኑ ለማረጋገጥ መልእክተኛ ይምጣ ልኝ ሳትል እርስዋ ራስዋ ፈጥና በመነ ሣት በእግር ጉዞ ጋራውን ዞራ ወንዙን ተሻግራ ኤልሳቤጥ ካለችበት ሥፍራ በመድረስ ያሳየችው ትሕትና ያስመሰ ገናት መሆኑ በሉቃስ ፩ ፡ ፴፱ - ፶፭ ተመ ዝግቦ ይገኛል ።

ዘግየት ብሎም ቃለ አብ ክርስቶስ የዓለም መድኅን ሆኖ ከርስዋ ከተወለደ በኋላ መላእክትና እረኞች ተባብረው ከዘመሩባት ከዚያች የእንስሳት በረት እስከ ግብጽ ስደት ፣ ከስደትም መልስ እስከ ናዝሬት ፣ ከዚያም እስከ እግረ መስ ቀሉ ድረስ ከልጇዋ ከወዳጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሳትለይ ለብዙ ፀዋትወ መከ ራና ፣ ለመሪር ሐዘን ሳትበገር በመኖር ዋ መንፈስ ጠንካራነትዋ ለክርስቲያ ኖች ሁሉ መልካም አርአያና ምሳሌ ይሆን ዘንድ ተጽፎአል ።

ከዚህም ሁሉ የምንማረው ብዙ ቁም ነገር አለ ፣ ይኸውም እመቤታችን ቅ/ ድ/ ማርያም በሕይወትዋ ዘመን ሁሉ ከልጅዋ ከወዳጅዋ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሳትለይ ድንቅ ሥራውን ሁሉ በማየት የቃሉን ትምህርት በመስማት ከቅዱሳን ሐዋርያት ከሳባ አርድእትና ከሠላሳ ስድስቱ ቅዱሳት አንስት ጋር ለጸሎት በመትጋት ምን ያህል ትተባበር እንደ ነበር ክርስቲያን ሁሉ ሊያስተውለው ይገባል ። -የሐዋ. ፩፡፲፭)

ስለዚህም ጠቅላላ ሕይወትዋ በቅድ ስና የተሞላ በጽኑ እምነት ታንፃ በመል ካም ሥነ ምግባር ያጌጠ ታሪክ ያላት ፍጽምት በመሆንዋ ከዚያ ሁሉ ፃማ ሊያሳርፋትና ከሞት ወደ ሕይወት ሊያ ሻግራት የአምላክ፣ፈቃድ መሆኑን የተ ረዱት አይሁድ የሚያደርጉት ቢያጡ አስከሬንዋን በእሳት ለማቃጠል የገመ ዱት ሴራ ውጤት አልባ ሆኖ ቀረ ። እነሶፎንያስ ሊያቃጥሉት የነበረውን አስከሬንዋን የእግዚአብሔር መልአክ ነጥቆ ወስዶ በገነት ዕፀ ሕይወት ሥር አኑሮት ነበርና ነው ።

ለቅዱሳን ሐዋርያትም ይህ ምሥጢር ተሠውሮባቸው ከጥር እስከ ሐምሌ ወር በመቆየቱ አዝነው ከነሐሴ ፩ ቀን ጀምሮ የሁለት ሣምንታት ጾምና ጸሎት አወጁ። ከሱባኤውም ፍጻሜ በኋላ መልአኩ አስከ ሬንዋን አምጥቶ አስረከባቸው ። ታዲያ ስምንት ወራት ያህል የቆየው አስከሬን ምንም ሳይለውጥ ትኩስ ሬሣ ሆኖ አግኝ ተውት መቃብር ምሰው በክብር እንዲ ያርፍ አድርገውት ነበር፣ያን ሁሉ ፀዋት ወመከራ በአሸናፊነት መውጣትዋን የተ መለከተ አምላክ ግን የዚያች ፍጽምት ቅድስት ድንግል ማርያም ሥጋ በመቃ ብር ፈርሶ እንዲኖር አልፈለገም ። እንደ ገና ቅድስት ነፍስዋን ከሥጋዋ በማዋ ሐድ ከነሕይወትዋ በይባቤ መላእክት ወደሰማይ እንድታርግ አደረገ ። ይህም ሁሉ እርሱ ራሱ ከሙታን ተለይቶ በተ ነሣ በአርባኛ ቀን ለፈጸመው ዕርገት ክብር በመሆኑ በሙታን ትንሣኤ ለምናም ንና የሚመጣውንም ሕይወት ተስፋ ለምናደርግ ተከታዮቹ ሁሉ አማናዊ መርህ ነው ።

ስለዚህ ሞትም ሆነ ሕይወት ሁለቱም እንደ አንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታ የሚ ቆጠሩ ስለሆኑ ሞት የክርስቲያኖች ማስፈራሪያ ሊሆን አይችልም ። የእመ ቤታችንን አርአያና ምሳሌነት በመከ ተል በእምነት ጸንተው እስከ ቀራንዮ መስቀል መንዝ ከሕይወት ወደሕይ ወት መሸጋገሪያ ድልድያችን ነው ። የሥጋ ሞት ክርስቲያኖች ሁሉ ወደክርስ ቶስ የሚያርጉበት መሰላል ነው ። ክርስ ቲያኖች ሊፈሩትስ የሚገባ ከእግዚአብ ሔር የሚያርቅ ኃጢአት መሥራትን ብቻ ነው ተብሎ ተጽፎአልና ። (ራእ ፳፩ ፡ ፰)

ሞቶሙስ ለጻድቃን ሕይወቱሙ ውእቱ የጻድቃን ሞታቸው ዕረፍትና ሕይወት ይሆንላቸዋል ተብሎ የተጻፈ ውም ስለዚህ ነውና ።

ቄ/ መክብብ አጥናው

# የግብርና በረከት

ከገጽ ፲፯ የዞረ

አርሶ አደር በተለይ የእንስሳት እርባ ታን የሚከታተሉ የራሳቸው ዘር እያመ ረቱ በመጠቀም ላይ ይገኛሉ ።

ለልዩ ዓመታት በገበሬው አካባቢ የከብት ድንች ምርት ክትትሉ በተደረ ገው ጥናት መሠረት በአማካይ ውጤት እስከ ፳ ቶንስ በሄክታር እንደሚደርስ ተደርሶበታል ።

## ፪.የከብት ድንች (ፎደር ቤት)

አመራረትና አጠቃቀም ፣

የከብት ድንች ምርት ክትትሉ በተደረ ገ ለወተት ላሞችና ለእርሻ በሬዎች ለበጋ ወራት በመኖነት የሚያገለግል ውሃ አዘል የሥራ ሥር ቤተሰብ ነው ።

የከብት ድንች ለማምረት የሚከተ ሉትን ዘዴዎች መጠቀም ያሻል ።

ሀ. የአየር ጠባይ የመኖ ዕፅዋትን ምርት ከሚወስኑት አንዱ የአየር ጠባይ ስለሆነ ለከብት ድንች የሚስማማው ጠባይ ቀዝቀዝ ያለ ይሆናል ።

ለ. ማሣ አመራረጥ የከብቶች ድንች ለማምረት እንደ ማናቸውም የሰብል እህል ጥንቃቄ ስለሚያስፈልገው ለም ማሣ ያስፈልጋል ። በረግረግ ቦታዎች መዘራት የለበትም ። በቂ ዝናብ ያገኘና ለም አፈር ያለው ማሣ ይመረጣል ።

ሐ. ማሣ ማዘጋጀት የበልግ ዝናም ከመ ጀመሩ በፊት ወይም ልክ እንደ ጀመ ረ ማሣውን በማረስ ፡በመከስከስና በማለስለስ ማዘጋጀት ይኸም የሚደ ረግበት ምክንያት አረሞችን ለመከላ ከልና በአፈር ውስጥ አየርና ውሃ በደንብ እንዲተላለፍና ዕድገትን እንዲያፋጥን ይረዳል ።

መ. የማዳበሪያ አጠቃቀም ማዳበሪያ ለመኖ ዕጽዋት ዕድገትና የምግብ ጥራት ስለሚረዱ በተገኘው ጥናት መሠረት ፩፻፶ - ፪፻ ኪሎ በሄክታር ፲፰ ፡ ፵፮ መጠቀም ይቻላል ።

ማዳበሪያው ዘሩ ከመዘራቱ በፊት ከአፈር ጋር መዋሃድ አለበት ።

ሠ. የዘር ጊዜ የከብት ድንች የመጀመ ሪያው የበልግ ዝናም እንደጀመረና አስተማማኝ ሆኖ መገኘቱ ሲረጋገጥ መዝራት ይቻላል ። አንዳንድ ጊዜ የበልግ ዝናም ስለማያስተማምን ምንም እንኳን የምርት ልዩነት ቢኖ ርም ትልቁ የዝናም ጊዜ ሲጀምር ባፋ ጣኝ መዝራት ሌላው አማራጭ መን ገድ ይሆናል ። የዘር መጠን በሄክ ታር ፰ - ፲ ኪሎ ነው ።

በመስመር ሲዘራ በየመስመሮቹ መካከል ያለው ርቀት ፵ ሳንቲ ሜት ር ሲሆን በመስመሮቹ ውስጥ በእያ ንዳንዱ ዕጽዋት መካከል የ፳፭ ሳንቲ ሜትር ርቀት መኖር አለበት ።

ወደ ገጽ ፳፫ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ተክለ ሃይማኖት ሐዋርያ

የኢትዮጵያ ሐዋርያ ጻድቁ አቡነ ተክለሃይማኖት ከአባታቸው ከቅዱስ ፀጋ ዘአብና ከእናታቸው ከቅድስት እግዚእ ሃረያ ከተወለዱ ጊዜ ጀምሮ የዓለም ብርሃን በመሆን እግዚአብሔርን በማገል



ተልቁ ፣ ኢትዮጵያዊ ፣ ጻድቅ ፣ አቡነ ፣ ተክለ ፣ ሃይማኖት ።

ገል እንደ ነቢያት ትንቢት በመናገር እንደ ሐዋርያት ዙሮ በማስተማር እንደ ሰማዕታት ልዩ ልዩ መከራ በመቀበል ለኢትዮጵያ ሕዝብ ያደረጉትን ትሩፋትና የፈጸሙትን ገቢረ ተአምር በአሁኑ ጊዜ ያለሰው አንደበት ተናግሮ አይጨርሰውም በጽሑፍ ሰሌዳም አስፍሮ ሊወስነው አይችልም በገድላቸው እንደ ተጻፈው ከኀርማ ወዲህ ያለው የሸዋ ምድር እስከ ደቡብ መጨረሻ ያለውን ክፍለ ሃገር ጨምሮ ከእግዚአብሔር እድል ፈንታ ሁኖ የተሰጣቸው ሀገረ ስብከት ሲሆን በሁለተኛው ደረጃ ብዙ ሕዝብ አስተምረው አሣምነው አጥምቀው አምልኰተ ባዕድን አጥፍተው አምልኰተ እግዚአብሔርን በማስፋፋት ክብራቸውን የገለጹበትና ብዙ ተአምራት ያሳዩበት ሀገር በቀድሞው ቤተ አምሃራ በዛሬው ወሎ ክፍለ ሃገር ያማራ ሣይንት ወረዳ ነው ።

ይኸውም በመጀመሪያ ከነበሩት ጳጳስ አቡነ ጌርሎስ መአርገ ዲቁናን ተቀብለዋል ። ሊቀ ጳጳሱ አቡነ ጌርሎስ የነበሩት በዚሁ በአማራ ሣይንት ወረዳ ልዩ ስሙ የገዛዛ ማርያም ይባላል በዚችም ቤተ ክርስቲያን ከአቡነ ጌርሎስ ጋር ስድስት ጳጳሳት የተቀበሩባት መሆኑን ታሪክ ይናገራል ፣ ከዚህ በኋላ ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የአቡነ በጸሎተ ሚካኤል ደቀ መዝሙር ሆነው ድውይ በመፈወስ ፣ ለምጽ በማንፃት ፣ ሙት በማንሣት ፣ አጋንንት በማውጣት ፣ብዙ ግቢረ ተአምራት በማድረግ አስር ዓመት ከአንድ ወር በአማራ ሣይንት መኖራቸውን ብፁዕ አቡነ ዮሐንስ ከማጠንቀቀው የፃፉት ገድለ ተክለሃይማኖት ይናገራል፣በአማራ ሣይንት ካደረጉት ብዙ ተአምራት ሁለቱን እንጠቅሳለን አንደኛ ማየ ረድኤት ጸበል በማፍለቅ ቸር ተክል ማርያም ከተባለችው ቤተ ክርስቲያን አጠገብ ከሚገኘው አንድ ታላቅ ዋርካ ስር ሆነው ሲጸልዩ መጋቢት ሃያ ቀን ከደረቁ አለት ድንጋይ ላይ ጸበል ፈልቆ እስከ መጋቢት ሃያ አራት ቀን ቆይቶ ደርቆ ነበር ይህ የሆነው ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በነበሩበት ዘመን ሲሆን ከዚያ ወዲህ ግን ይህ ገባሬ ተአምር ጸበል ጊዜውን እየጠበቀ በየዓመቱ መጋቢት ሃያ ቀን ይፈልቅና መጋቢት ሃያ አንድ ቀን ከቅዳሴው በኋላ ይደርቃል ። ይኸውም ታሪክ ነበር ሳይሆን ዛሬም በአሁኑ ጊዜ እየተፈጸመ ስለሚታይ ሕዝቡ በረድኤታቸው ከሃገሩ ላይ ባለ መሬቱ በአካባቢው ያሉ ምዕመናን የጻድቁን አማላጅነት በማመን የእግዚአብሔርን ቸርነት እያደነቁ ይኖራሉ ።

፪ ሙት በማንሣት የተደረገ ተአምር ሃገሩ አሁንም ያው አምሃራ ሳይንት ነው ብፁዕ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ምሥካበ ቅዱሳን ወደ ተባለችው ገዳም ሂደው ከሰው ተለይተው በአንድ ዋሻ ውስጥ ሁነው በሚጸልዩበት ጊዜ ለብዙ ዘመን እንደ መጻጉዕ በደዌ ቁራኝነት ተይዞ ከአልጋ ላይ ተጣብቆ የሚኖር አንድ በሽተኛ ነበር ሞተና ዘመዶቹ ሊቀብሩት ሲወስዱት እንደ አጋጣሚ ጻድቁ በሚጸልዩበት ዋሻ በር አስከሬኑን አሣርፈውት ሣለ እሬሣው መግነዝ ፍቱልኝ ሣይል እራሱ መግነዙን ፈትቶ አፈፍ ብሎ ተነስቶ በናይን ወለደ መበለት የኢያኢሮስን ልጅ ፣ የአራት ቀን ሬሣ አላዛርን ያስነሣ እግዚአብሔር እኔንም ከሞት አስነሣኝ እያለ ያመሰግን ጀመር የሕዝቡም ልቡና በአቢይ ፍርሃት በፅኑ ድንጋፄ ተዋጠና ማን አስነሣህ ብለው ቢጠይቁት በኤልያስ አድሮ አንድ ምውት ፣ በኤልሣዕ አድሮ ሁለት ምውት ያስነሣ አምላክ በተክለሃይማኖት ላይ አድሮ እኔንም በሕይወት አስነሣኝ እርሱም የጨለማው ክብደት በማይነቃነቅ ዋሻ ውስጥ የሕይወት ብርሃን ከሆነው ከኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ቆሟል አላቸው ሕዝቡም እንደገና ወደየቤታቸው ተመልሰው በዙሪያው ያሉ ድውያንን በአልጋ እያመጡ በዋሻው በር ላይ አሰፈሯቸው ጻድቁንም ወጥተው እንዲያድኑላቸው ለመኗቸው የእግዚአብሔር ሃይል

ያልተለያቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ሕሙማኑ ወደአሉበት ወጥተው ሁሉንም ካለባቸው ደዌ አዳኗቸው ያችም ዕለት የመዳን ቀን ናትና ሕይወቱን ሳያገኝ የተመለሰ አንድም ሰው አልነበረም ጌታ ለደቀ መዛሙርቱ በዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፬ ቁጥር ፲፪ እውነት እውነት እላችኋለሁ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል ብሎ የተናገረው ለእውነተኛው መልእክተኛው ተክለሃይማኖት በዚያች ሰዓት ተፈጸመ ከሞት የተነሣውንም ሰው ሃራ ኢየሱስ ብለው ሰይመው ከደቀ መዛሙርቱ ጋር ቆጥረው የትምህርተ ወንጌል ተካፋይ በማድረግ አሥራ ሁለት ዓመት አስከትለውት ሂደዋል ሃራ ኢየሱስም ዕለተ ሞቱ በሚደርስበት ጊዜ ወደምሥካበ ቅዱሳን ተመልሶ በተፈጥሮ የተሰጠውን ዕድሜ ጨርሶ በክብር እንዳረፈ ዜና መንፈሳዊ ይናገራል ። ምሥካበ ቅዱሳንን ካነሳን ዘንድ ትርጓሜውን በመጠኑ መግለጽ ያስፈልጋል ምዕራፈ ቅዱሳን የቅዱሳን ማረፊያ ማለት ነው በገድል ተቀጥቅጠው የሚኖሩ ሰባ ሁለት ቅዱሳን የተጋድሎ ጊዜያቸውን ፈጽመው ስለአረፉበት ምስካበ ቅዱሳን ተብላለች በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ማርያም ስም የታነፀች ቀዳሚት ቤተ ክርስቲያን ነች የዚያ ደብርም ቅድምና በ፱፻፲ በዘጠኝ መቶ አስር ዓመተ ምሕረት ከአፄ ድልነ አድ ዘመን ሲያያዝ መጥቶ በአንድ ሺ አራት መቶ አርባ ስምንት ዓ.ም. በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፈቃድ ወደ ገዳምነት ተለውጠ የንፁሐን መነኮሳት መኖሪያ ገዳም እንዲሆን ተወስኗል ይሄውም ገዳም በአቡነ በጸሎተ ሚካኤልና በሐዋርያው አቡነ ተክለሃይማኖት ቃል ኪዳን ጸንቶ ስለሚኖር ታላላቅ መምህራንና አበው መነኮሳት ይገኙበታል ።

እንግዲህ ከምዕራፈ ቅዱሳን ተነስተን ዜና መንፈሳዊን በመከተል ወደ ቀደመ ነገራችን እንመለስ ሐዋርያው አቡነ ተክለ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ሰሜን የነበረውን የወንጌል ትምህርት ክፍለ ዘመን ጨርሰው ወደ ደቡብ ሲመለሱ በአንድ ሽ ሁለት መቶ ሰባ ሰባት ዓ.ም. በአፄ አግብአ ጽዮን ዘመነ መንግሥት መላ የሸዋ ሕዝብ ያስተማሩትን ትምህርት የሠሩለትን ሥርዓት ጠብቆ በምግባር ፣ በሃይማኖት ጸንቶ በፍጹም የእግዚአብሔር ተገዥ ሁኖ ስለአገኙት በጣም ደስ አላቸው ፈጣሪያቸውንም አመስገኑ በአንጻሩ ከአዋሽ ባሕርና ከጊቤ ወንዝ ማዶ ካሉት አህጉር ሁለት ተለይተው ከአምልኮተ እግዚአብሔር ወደ አምልኮተ ጣኦት ከገቢረ ጽድቅ ወደ ገቢረ ሃጢአት ተመልሰው የቤተ ክርስቲያንን መምህራን እያሳደዱ ሌሎች ነቢያተ ሐሰትና ክህናተ ጣኦት አቁመው በእነሱ ትእዛዝ እየተመሩ የጥንቱን ቤተ መቅደስ አፍርሰው የጣኦት ቤት ሰርተው እግዚአብሔርን እየበደሉ እራሳቸውን ለሰይጣን ተገዥ በማድረግ ይጠቅመናል ብለው ያመኑበትን ለመስዋዕት የሚሆን ብዙ የግመልና የሪያ መንጋ ስብስበው ስለአገኙዋቸው ከባድ ሐዘን ወደቀባቸው ይልቁንም በንጹህ መስዋዕት ፈንታ አስጸያፊ ርኩስ ነገር ለመስዋዕት አቅርበው በማየታቸው ወደ ፈጣሪ አመለከቱ፡ ምክንያቱም በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ሃያ አራት ቁጥር አስራ አምስት እንግዲህ በነቢዩ በዳንኤል የተባለውን የጥፋት እርኩስ በተቀደሰው ስፍራ ላይ ቆሞ ስታዩ አንባቢው ያስተውል ያለውን ቃል በማሰብ የቅዱሳን ዓለም የነበረች ሕይወታቸው ለፍጻሜ እንደተቃረበች በማወቅ ነው

ይቀጥላል

አለቃ ኤልያስ



www.ethiopianorthodox.org

# መመስከር እንደ ጊዮርጊስ

የምስክርነት ዓይነት ብዙ ነው ራሳቸውን በመውደድ ሌላውን በመጥላት ጻድቁን ለመኰነን ኃጥኡን ለማዳን በገንዘብ ተገዝተው ያልሰሙትንና ያላዩትን በማደባለቅ የሚመሰክሩ አሉ ። ከዚህም ሌላ እውነትን በኃሰት ለውጠው ባልተጨበጠ ሁኔታ ለመኖር በሥጋ ዘመድ ለማብዛት በቂም በበቀል እውነተኛውን ሰው ለማጥፋት የሚመሰክሩ እንዳሉ ከጥንት ጀምሮ በታሪክ የተረጋገጠ ነው ።

የቅዱስ ጊዮርጊስ ምስክርነት ግን ከዚህ የተለየ ነው ዓይን ያላየው ጆሮ ያልሰማው ልዑል እግዚአብሔር በተለየ ምስጢር ለወዳጆቹ ያዘጋጀው ዕሡብ ድንቅ የሆነ አስገራሚና አስደሳች የሆነው ምስክርነት ነው ። ለዚህም ምስክርነት ቅዱስ ጊዮርጊስን የጠራው ማን ነው ? የመሰከረውስ ለማን ነው ? ለምስክርነት ከመጠራቱ በፊት የት ነበር ? ያስመሰከረው ዳኛ ማን ነበር ። ?

ቅዱስ ጊዮርጊስ ለዚህ ምስክርነት ከመጠራቱ አስቀድሞ የነበረው በእናት በአባቱ ቤት ነው አባቱ ዞሮንቶስ (አንሰጣስዮስ) ይባላል እናቱ ቴዎብስታ ትባላለች አገራቸው በእስያ አህጉር በቀጳዶቅያ አውራጃ ልዩ ስሟ ልዳ ትባላለች እናቱና አባቱ በሕግ በሥርዓት ተጋብተው ቅዱስ ጊዮርጊስን ወልደው የቅዱስ ጊዮርጊስ ዕድሜው ፳ ዓመት ሲሆነው አባቱ ሞተ ።

አባቱ በሹመት የበለጸገ ሀብታም ነበርና ቅዱስ ጊዮርጊስም የአባቱን ሹመት ለመውረስና ለመረከብ ፈረሱን በቅሎውን አስጭኖ ብዙ ሠራዊት አስከትሎ ወደ ንጉሡ ወደ ዱድያኖስ አደባባይ ሄዶ በዚህ አደባባይ ላይ ብዙ ሕዝብ ንጉሡ ከሀዲ ነብርና ለአቆመው ጣዖት ሲሰግድ ሲንበረከክ አይቶ ተበሳጨ ምክንያቱም ለማዳን ለመግደል ለመስጠት ለመንሳት ችሎታ ያለውን አምላክ ባለማወቅ ለማያድንና ለማይሰማ ጣዖት ሕዝቡ ሲሰግድ በማየቱ ነው በዚህ የተነሳ ቅ/ ጊዮርጊስ ከሹመት ከሽልማት ከዓለም ክብርና ጌጥ ጋር ሆኖ እውነት መመስከር የማይቻል መሆኑን ተገንዝቦ ሹመቱን ንብረቱን ክብሩን አምዘግዝጎ ጥሎ ፈረሱንና ጦሩን ብቻ ይዞ ተነሳ በዚህ ሁኔታ እውነቱን ከሀሰት ለይቶ እንዲመሰክር የጠራው የክርስቶስ ፍቅር ነው ።

የመሰከረው ስለ እግዚአብሔር አዳኝነት ብቻ ነው ። እውነትን ለመመስከር የቆመበት አደባባይ የክርስቶስ መከራ መስቀል ነው አስመስካሪው ክፍል በድንቁርና መጋረጃ የተሸፈነው የሀሰት አባት የጽድቅ ጠላት ዱድያኖስ ነበር ቅዱስ ጊዮርጊስ በተወለደ በሃያ ዓመቱ የዚህን ዓለም ኑሮና ክብር ንቆ በወዲያኛው ዓለም ለውጦ ሊመሠክር በጀመረበት ቀን አልተፈጸመለትም ነገሩ እየተጓተተ ከቀን ወደ ቀን አመፅ ፣ በደል ፣ እየተጨመረ ግፍ እየበዛ ሄደ ።

እርሱም የበለጠ በሚያየውና በሚሰማው በእውነት የምስክርነት ቃሉን እየጠናከረ ግፈኞችን በማያወላውል የምስክርነት ቃሉ እያሳፈረ ፯ ዓመት ሙሉ ቆይቶአል ። በ፯ ዓመት ውስጥ አንድም ሽፋጮችንና አመፀኞችን ሳያስደነግጥና የተበደሉትንና ፣ የተገፉትን በሚሰጠው የምስክርነት ቃል ሳያረካና ሳያስደስት የዋለበት ቀን ወይም ጊዜ አልነበረም የመጨረሻውን የምስክርነት ቃል የሚፈጽምበት ጊዜ እየተቃረበ በሄደ ጊዜ በ፯ኛው ዓመት በአደባባይ የምስክርነት ቃሉን ሲሰጥ ፳፻ ሰዎች በቅዱስ ጊዮርጊስ ምስክርነት አምነው ከአምልኮተ ጣዖት ወደ አምልኮተ እግዚአብሔር ስለተመለሱ በከሃዲው ንጉሥ በዱድያኖስ ትእዛዝ በሰይፍ ታርደው የሰማዕትነት አክሊል ተቀዳጅተዋል ፤ የንጉሡ ሚስት እለ እስክንድርያ ጊዮርጊስ ሲመሰክር ሰምታ ለንጉሡ የክርስቲያኖች አምላክ እግዚአብሔር ኃያል ነው ጊዮርጊስም የሚመሰክርለት ስለሆነ አታስቀየው ብላ በአሽከሮቹ ፊት ስለዘለፈችው በሰይፍ እንድትቆረጥ ዱድያኖስ አዘዘ ።

ቅ/ ጊዮርጊስም አይዞሽ ጽኚ በርቺ ባላት ጊዜ መከራውን ሳትሰቀቅ ተቀብላ የመጨረሻውን የሞት ፅዋፅ በሰይፍ ተቀብላ የክብር አክሊልን ተቀብላለች የንጉሡ ሚስት ሃይማኖቷን ለውጣ በጊዮርጊስ ምስክርነት በእግዚአብሔር ስለአመነችና ተሰይፋ ስለሞተች ፸ ነገሥታት መክረው ዱድያኖስ ጊዮርጊስን በሰይፍ እንዲያስቆርጠው ማለዱት ጊዮርጊስም በዚህ ጊዜ እንደ ታሠረ ወደፈጣሪው በጸሎት ለመነ እንዲህ ሲል አቤቱ ፈጣሪዬ ኤልያስጸልዮ እሳት ከሰማይ አውርዶ ፻፶ ሰዎችን እንዳቃጠለ እኒህን ከሃዲዎች ፸ውን ነገሥታት እሳት ከሰማይ ወርዶ ተቃጥላቸው አለ ጸሎቱን እንደጨረሰም እሳት ወርዶ በከሀዲው በዱድያኖስ ቤት ውስጥ ሲበሉ ሲጠጡ ሳሉ ሠራዊቱ በሙሉ እንደ ተሰሰሰቡ ተቃጠሉ ቅዱስ ጊዮርጊስም የተደረገለትን ቸርነት አይቶ የ፯ ዓመቱን የምስክርነት ተጋድሎ ሚያዝያ 23 ቀን ፈጽሞ የደከመበትንም የምስክርነት ዋጋ ፯ የብርሃን አክሊላት ከፈጣሪው ተሸለመ እንግዲህ እኛም ሁላችን ክርስቲያኖች በእውነት መሰከረን የማያልፈውን የመንግሥተ ሰማያት ዋጋ እንደ ጊዮርጊስ ከፈጣሪያችን ለመቀበል ያብቃን ።

ቄስ ገብረ መስቀል ቸኮል



# ስብከተ ወንጌል

ሰባክያነ ወንጌል ያለ ዳቦ ምድራውያን መላእክት ሆነው እንዲኖሩ የሚሹ አይታጡም ። ሰባክያነ ወንጌል በንጽህናቸው በቅድስናቸው ለምዕመናን አርአያ በሚሆኑበት ሥራ ሁሉ ምድራውያን መላእክት ሊሆኑ ይገባል ፣ ለዚህም ተጠርተዋል ።

ያለምድራዊ ዳቦ ሊኖሩ ግን አይችሉም ፣ አንድ ባለቅኔ በአንድ ታላቅ በዓል ላይ ሲቀኝ "ኢትቀውሞ ዘእንበለ ሥጋ ማርያም ነፍስ" ያለ ሥጋ ማርያም ነፍስ አትቆምም በማለት ተቀኝቷል ሥጋ ያለነፍስ ፣ ነፍስም ያለሥጋ በዚህ ዓለም ጸንተው ሊኖሩ አይችሉም።

ሰባክያነ ወንጌልም ሆነ በአጠቃላይ [illegible] ክርስቲያን ሊቃውንት ያለምድራዊ ዳቦ [illegible] እንደሚገባቸው አድርገው የሚናገሩ ፣ የማያስቡላቸው ፣ የማይራሩላቸው አይታጡም ።

ጌታችን መድኃኒታችንና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጠውንም ትእዛዝ ምክንያት በማድረግ ካህናትን ጦም አዳሪዎች እንዲሆኑ ይተቻሉ ። "ወርቅ ወይም ብር ወይም ናስ በመቀነታችሁ ወይም ለመንገድ ከረጢት ወይም ሁለት እጅ ጠባብ ወይም ጫማ ወይም በትር አትያዙ ። ለሠራተኛው ምግቡ ይገባዋልና (ማቴ ምስ ፲ ፣ ፱ - ፲)

ይህን መሠረት በማድረግ የእግዚአብሔር መልእክተኛ ጦም ይደር ፣ ምንም አይኑረው ይላሉ ፣ ይህ ታላቅ የጌታ ቃል ሐዋርያት ሀብት በማከማቸትና ግለኞች በመሆን የተላኩበትን ዓላማ እንዳይዘነጉ ፤ በሥጋዊ ጥቅም እንዳይጠመዱ አስጠንቀቀ እንጂ የዕለት ጉርስ ፣ የዓመት ልብስ አይኑራችሁ አላለም ፣ ቤተ ክርስቲያን ምድራዊትና ሰማያዊት እንደመሆኗ መጠን በውስጧ ላሉ የጌታን ስም ተሸክመው ለመሄዱ መልእክተኞቿ ራሳቸውንና ሌሎቹንም የሚረዱበት ገንዘብ ልብስና መጓጓዣ ያስፈልጋቸዋል ። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱ ለሥጋዊ ምቾት ራሳቸውን እንዳያስገዙ አዘዛቸው እንጂ ምግብ ሳይመገቡ የረሃብ አለንጋ እየገረፋቸው በችግር ተቆራምደው እንዲኖሩ አላዘዛቸውም እንዲያውም "ለሠራተኛ ምግቡ ይገባዋልና" ነው ያለው ።

የምዕመናን ሀብት የእነርሱ ጭምር መሆኑን ሲያጠይቅ በየደረሳችሁበት ይመግቡአችሁ ብሏል ። ይህም በጌታ ትእዛዝ መሠረት ሲፈጸም ቆይቷል ፤ ወደፊትም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ በእውነተኞች ምዕመናን ዘንድ ይፈጸማል ፣ ይሁን እንጂ የዓለም መልክ [illegible] ተለወጠ ሄዷል ፤ ወደየግለሰቡ [illegible] ገብቶ ዳቦ አምጡ ማለት [illegible] ገንዘብን [illegible] ዘጋጅው ዳቦ በአንተ [illegible] ችልም ። ዓለም ገንዘብ እየ[illegible] ታዲያ ወንጌል ያለ ዳቦ [illegible] በከ ? [illegible] ዛሬ በበቅሉና [illegible] ጆርባ ተጉዞ የሚዘልቅ አለ [illegible] ገዱ ሁሉ በሰማይና በምድር [illegible]

ፍጥነት ባላቸው የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሆኗል ፤ በእነርሱም ለመጓዝ ገንዘብ ያስፈልጋል "ገንዘብ ካለ በሰማይ መንገድ አለ" ተብሏልና ። የሐያኛው ምዕት ክፍለ ዘመን ሁኔታ የገባቸው የወዲያ ማዶ አብያተ ክርስቲያን ካህናት ለምዕመናን ችግሩን እያስረዱ ስብከተ ወንጌል ለመላ ዓለም ምዕመናን የሚዳረስበትን ፣ ሃይማኖት የሚጸናበትን ምግባር የሚቀናበትን መንገድ ከቀየሱ ቆይቷል ። ታላቋ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ሊቅ ፣ የጸዋትወ ዜማና የቅኔ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ "ወረድየብሔረሮሜለቤተክርስቲያን ርኢክዋበማለት እንደዘመረና እንደጻፈው ሁሉ ብዙዎች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ልጆች አምስቱን ክፍላተ ዓለም በመዘዋወር መጎብኘት ችለዋል በዚያ ያሉት አብያተ ክርስቲያን ስብከተ ወንኬል እንዴት እንደሚስፋፋ ፣ ትምህርት ቤቶችን እንዴት እንደሚያቋቁሙ ፣ ራሳቸው የዓመት ልብሳቸውን ከየት እንዴት እንደሚያገኙ ተመልክተዋል ። ባለፈው ሌሊት በሕልሜ ታላቅ አውሎ ነፋስ ሲነፍስ አየሁ ፤ እሳት በኃይል ሲነድና ሲገር ተመለከትሁ ፣ ሰማይ ሊደረባ ፣ ምድር ሊገለበጥ ነው ወዮላችሁ ካለ በኋላ በማሳረጊያው ልብሱን ዘርግቶ ገንዘብ አምጡ በማለት የሚያታልል ቀጣፊ ሰባኪ የለም ። በወዲያይቱ ቤተ ክርስቲያን ሁሉም በሥርዓትና በወግ ፣ በመርሐ ግብር ይካሄዳል ። በወዲያይቱ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞች የሚተዳደሩት ከምዕመናን በተሰበሰበው በተጻለየበት ሙዳዩ [illegible] ፤ የአስራት አስተዋጽኦና በየ[illegible] በሚሠሩት የሥራ ውጤት በተገኘው ገንዘብ ነው ።

ምዕመናን ወንዶችም ሴቶችም በዕለተ ሰንበትም ሆነ በማንኛውም በዓል [illegible] እስከ ካልገጠማቸው በስተቀር ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው አይቀሩም ። ሲመጡም ለሙዳየ ምጽዋት የሚሰጥ ገንዘብ ሳይዙ አይመጡም። በቅዳሴ ጸሎት ጊዜ በሙዳዩ ምጽዋት በጣም ብዙ ገንዘብ አብያተ ክርስቲያን ያገኛሉ ።

ገንዘቡ ከምዕመናን የሚሰበሰበው ፍሬ ቅዳሴ ሊጀመር ሲቃረብ ነው ። የሙዳዩ ምፅዋቱን ሳጥን ይዘው የሚዞሩት ለዚሁ የተዘጋጁ ልብሰ ተክህኖ የለበሱ የዲቁና ሥልጣን ያላቸውናቸው ። ከተሰበሰበ በኋላ ወደቅድስተ ቅዱሳን ይቀርባል በገንዘቡም ላይ መሪው ካህን ይጸልይና በመንበሩ አንጻር ቆሞ ምዕመናንን ይባርካል ።

በጸሎተ ቅዳሴው ፍጻሜ የቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪና ከሰበካ ጉባኤ አባላት ውስጥ የሚመለከታቸው በአሉበት ተቆጥሮ የገንዘቡ መጠን በመዝገብ ይጻፍና ወደባንክ ይገባል ።

የገንዘቡ አጠቃቀም ፣



www.ethiopianorthodox.org

ሀ/ ገጠራቱ ቤተ ክርስቲያን ለወረዳው ቤተ ክህነት ፣

ለ/ የወረዳው ቤተ ክህነት በውስጡ ካሉት አብያተ ክርስቲያን ካገኘው ለአውራጃው

ሐ/ አውራጃው ለሀገረ ስብከት መንበረ ሊቀ ጳጳስና

መ/ መንበረ ሊቀ ጵጵስናው ለመንበረ ፓትርያርክ አሥራት ያወጣሉ ፣ በአሥራት ከታች ወደላይ የመጣው ገንዘብ ደግሞ ከላይ ወደታች ይወርዳል ።

ሀ/ በመንበረ ፓትርያክ አስተዳደር ፣

ለ/ ለቅዱስ ሲኖዶስ የሥራ ማንቀሳቀሻ

ሐ/ ለቤተ ክርስቲያኒቱ የውጭ ጉዳይ መምሪያ

መ/ ለመንፈሳውያን ሴሚናሮችና ታላላቅ የቴአሎጂ አካዳሚዎች ይከፈላል ።

በገጠር ካሉት ምዕመናን አነስተኛ በሆኑበት አካባቢ ያሉ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያን የሙዳየ ምጽዋቱ ገንዘብ ያንሳቸውና ለንዋየ ቅድሳትና ለሕንፃ ቤተ ክርስቲያን ማደሻ ገንዘብ ሊያጡ ስለሚችሉ ከታች ወደላይ ከመጣው ገንዘብ ለእንዲህ ያለው ፈጥኖ የሚደርስ ገንዘብ ይቀመጥና ከሀገረ ስብከቱ ሪፖርት ሲደርስ ገንዘቡ ከመንበረ ፓትርያርኩ ፈጥኖ ይላክና ከገጠሪቱ ቤተ ክርስቲያን ችግር ፈጥኖ እንዲወገድ ይደረጋል ።

ገዳማት ፤ የገዳማት መነኮሳት የሚኖሩት እየሠሩ ነው ።

ሀ/ በገዳማቸው ክልል ፍሬ የሚሰጡ አትክልትን እየተከሉ ፣

ለ/ ከብትና ንብ እያረቡ

ሐ/ እጅን የሚያስደስቱ ስዕሎችን እየሳሉ

መ/ ለአብያተ ክርስቲያናት የሚጠቅሙ ንዋያተ ቅድሳትን እያዘጋጁ

ሠ/ ለአብያተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደየደረጃቸው የሚሸለሙ ወይም የሚሸጡ የክብር መስቀሎችን እየቀረጹ በጣም ብዙ ገንዘብ ያገኛሉ ።

ረ/ በሙዳዩ ምጽዋትም ብዙ ገንዘብ የሚሰበሰብ ከመሆኑም በላይ እያንዳንዱ ገዳም የየራሱ ጥንታዊ ቅርስ ሙዚዬም ስላለው ቱሪስቶች ለጉብኝት ሲመጡ የሚገኘው ገቢም በጣም ብዙ ነው ። መነኮሳቱ በምጽዋት ባገኙት ገንዘብ ከመጠቀም ይልቅ ሠርተው ባገኙት መጠቀምን ይመርጣሉ ፣ የምጽዋቱን ገንዘብ ለእንግዳ ሲሰጡ በጣም ደስ ይላቸዋል ።

ይህም "ሥራቸው እንድ ስለነበረ በእነርሱ ዘንድ ተቀምጦ በአንድ ላይ እየሰሩ ሥራቸውም ድንኳን መስፋት ነበርና" የሚለውን ያሳስበናል (የሐዋርያት ሥራ ፲፰. ፫) ቅዱስ ጳውሎስና ሌሎችም ሐዋርያት ሥራ እየሠሩ ይጠቀሙ እንደነበረ ያመለክታል ።

አሁን ያለንበት ሐያኛው ምዕት ክፍለ ዘመን የባህል ቴአሎጂ ባህልና ክርስትና ፣ ልማድና ክርስትና የውጭ ባህልና ክርስትና የሚታገሉበት ዘመን ነው ። እንዲህ ያለውን ጥልቅና ምጡቅ መንገድ የሚመረምሩ ምዕመናንን በትክክለኛው የክርስትና መስመር የሚያሠማሩ ሊቃውንት ለቤተ ክርስቲያን በጣም ያስፈልጋሉ ፤ አንተ ከመለመን ታርፋለህ ተማሮችህ እየለመኑ ያበሉሃል የምንልበት ጊዜ አይደለም ፣ ቤተ ክርስቲያን በመጀመሪያ ስትመሠረት "በዚያን ቀን ሶስት ሽህ ያህል ነፍስ ተጨመሩ በሐዋርያት ትምህርትና በኅብረት እንጀራውንም በመቁረስ ፣ በጸሎትም ይተጉ ነበር" (የሐዋርያት ሥራ ፪. ፵፩ - ፵፪) ይላል ። ጥንታውያን ክርስቲያኖች የወንጌልን ትምህርት እየተማሩ በሕብረት እንጀራ ይቆርሱና ይመገቡ እንደነበር በግልጽ ተጽፏል ። ይህም የሚያመለክተው ወንጌል ከዳቦ ጋር መሆን እንዳለበት ነው ።

ወንጌል ከዳቦ ጋር እንዲሰምር በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ በመላዋ ኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያን የተዘራው ቃለ ዓዋዲ በየአህጉረ ስብከት ሲሠራበት ቆይቷል ። ግን አሁን በግንቦት ፳፬ እስከ ግንቦት ፳፰ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ድረስ "ወነአምን በአሐቲ ቅድስት ቤተ ክርስቲያን እንተ ላዕለ ኩሉ ጉባኤ ዘሐዋርያት" በሚል ርዕስ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ሊቀ መንበርነት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት የተካሄደው ብሔር አቀፍ አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ ወንጌል ከዳቦ ጋር እንዲራመዱ የሚያደርግ ተስፋ ያለው የፍሬው እሸት የታየበት ታላቅ ጉባኤ ነው ። የመጀመሪያውን እሸት ያቀረቡት የጎጃም የሸዋና የአዲስ አበባ አህጉረ ስብከት ሲሆኑ ሌሎችም የሰበካ ጉባኤውን በማቋቋም ያሳዩት የሥራ ፍሬ የሚያስደስት ነው ። ወንጌል እንዲሰበክ ፣ የቤተ ክርስቲያን ታላቅ ታሪክ እንዲቀጥል ከተፈለገ መንገዱ አሁን የተቀየሰው የሰበካ ጉባኤ መንገድ ነውና ሁሉም በየአቅጣጫው ሊበረታ ይገባል ።

ሊቀ ብርሃናት ሰሎሞን ገ/ሥላሴ



# ቤተ ክርስቲያን ባለፈው ዓመት

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ በአለፈው ዓመት ምን ልማት እንደተሠራ ምን ጉድለት እንዳለ የሚገመገምበትና የሚታሰብበት ወቅት ነው ። ይህም ሲባል በአለፈው ዓመት ጥሩ ሥራ ተሰርቶ ከሆነ ለሚቀጥለው ዓመት ከዚህ በበለጠ የተሻለ ለመሥራት የአለፈውን የሥራ ውጤት ዘወር ብሎ ማጤን ያስፈልጋል በአለፈው ዓመት ሥራው በጥሩ ሁኔታ ካልተሠራ ለሚቀጥለው ዓመት ይህ ችግር እንዳይቀጥል የሚወገድበትን መንገድ የሚፈለግበት ወቅት ነው ። በአለፈው ዓመት ስለነበረው ልማትም ሆነ ጉድለት ከታወቀ ጉድለትን አስወግዶ ለወደፊቱ በዕቅድና በፕላን ለመመራት ይቻላል ።

ሰውን አዋቂ ነው የሚያሰኘው ትልቁ ነገር የሚሠራውንና የሚያደርገውን አውቆ በትክክል መሥራት ሲችልነው፣ በአለፈው ዓመት ምን ሠራሁ ፣ ብሎ ራሱን ሲገመግምና ለወደፊትም ለሚሠራው ዕቅድና ፕላን ዘርግቶ በዕቅድ ሲመራ ሥራው የተስተካከለ ይሆናል ያለ ፕላንና ዕቅድ የሚሠራ ሥራ ግን ውጤት የለውም ዕድገትም አያስገኝም ።

እንግዲህ ቤተ ክርስቲያን በአለፈው ዓመት ስንል በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ምን ልማት ተሠራ ምን ዕድገትስ ተገኘ ብሎ መጠየቅ ያሻል በ፲፱፻፹፭ ዓ.ም.በ ቤተ ክርስቲያን ከፍተኛ የሆኑ ነገሮች ተሠርተው እናገኛለን ለዚህም የሥራ ዕንቅስቃሴ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በየቦታው እየተገኙ የሚሠጡት መመሪያና ትዕዛዝ ነው ።

ቅዱስነታቸው መስከረም አንድ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. የዘመን መለወጫ በዓልን ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በአስተላለፉት ቃለ ምዕዳን አዲሱ ዘመን የሰላም የጤንነት የሥራ እንዲሆንና በዓለም ሰላም እንዲሰፍን የዘወትር ጸሎታቸው መሆኑን አብስረዋል ።

ቅዱስነታቸው በዚሁ ወር መስከረም ፲፮ ቀን የሚከበረውን የደመራ በዐል ምክንያት በማድረግ በበዓሉ ቦታ ተገኝተው ለምዕመናን ቡራኬ በመስጠት በዐሉን አክብረዋል ።

በዚህ በአለፈው ዓመት በተለይ ትልቅ የሥራ ፍሬ ውጤት የሆነ ሥራ ተሠርቶአል ። ይህውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ሐዋርያዊ ድርጅት ይባል የነበረው ድርጅት መስከረም ፳ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. ፳ኛ ዓመቱን ድምቀት በአለው በዐል በአከበረት ወቅት ቅዱስነታቸው በበዐሉ ላይ በመገኘት በሰጡት ትዕዛዝና መመሪያ ከስብከተ ወንጌል ጋር በአንድ መምሪያ አብረው እንዲሠሩ በአዘዙት መሠረት ስሙም ከዚህቀን





ቅዱስነታቸው መመሪያ ሲሰጡ



www.ethiopianorthodox.org

ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ተብሎ እንዲጠራ ፈቅደዋል ። በትዕዛዙ መሠረት ከሕዳር አንድ ቀን ፸፩ ዓ.ም. ጀምሮ ሁለቱ ድርጅቶች ከላይ በተጠቀሰው ስም በመጠራት በአንድ መምሪያ ተጠቃለዋል ።

በሌላ በኩል ደግሞ ቅዱስነታቸው ሰበካ ጉባኤ እንዲጠናከር ፣ የፈረሱ አብያተ ክርስቲያናት እንዲታደሱ በሚሰጡት መመሪያ መሠረት በጎንደር ክፍለ ሀገር በደብረ ታቦር አውራጃ የምትገኘው ማኅደረ ማርያም ታድሳ ዕድሳቷ ስለአለቀ ቅዱስነታቸው በሕዳር ወር በቦታው ተገኝተው የማኅደረ ማርያምን መቅደሱን ባርከው ታቦቷ ወደመንበረ ክብሩዋ ከገባች በኋላ ለሕዝቡ ቃለ ምዕዳን ሰጥተዋል ከዚያም በዋንዛዩ የሚገኘውን ፍልውሐ በጐበኙበት ጊዜ ከዚያ ለሚገኙት ብዛት ላላቸው ምዕመናን ቤተ ክርስቲያን እንዲሠራላቸው ትዕዛዝ ሰጥተዋል ።



ሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ለአጠቃላይ ሰበካ ጉባኤ ንግግር ሲያደርጉ ።

ቅዱስነታቸው በዚሁ ወር ሕዳር፳፩ ቀን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርዕሰ አድባራት ሁና ለብዙ ዘመን በቆየችውና በታሪኳ በታወቀችው በአክሱም ጽዮን በበዐሉ ዕለት ከዚያ ለተሰበሰቡት በብዙ ሺህ ለሚቆጠሩት ምዕመናን ቃለ ምዕዳን በማስተላለፍ ቡራኬ ሰጥተዋል ችግርም ለደረሰባቸው ካህናትና ምዕመናን የገንዘብ ዕርዳታ እንዲደረግላቸው ትዕዛዝ ሰጥተዋል ።

ቤተ ክርስቲያን በልማት በኩል ለምታደርገው ዕንቅስቃሴ ቅዱስነታቸው በቦታው እየተገኙ መመሪያ ይሠጣሉ። በዚህም መሠረት በታኅሣስ ወር የጎፋ ቅ/ገብርኤል የዕደ ጥበብ ማሰልጠኛን ጐብኝተው ማሰልጠኛው እንዲስፋፋ ትዕዛዝ ሰጥተዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊት ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎቹ አብያተ ክርስቲያናት ጋር ባላት ግንኙነት መሠረትና በዓለም ቤተ ክርስቲያን ማኅበር አባልነቷ የዕርቧን ልዑካን የሥራ ልምድ ለመለዋወጥ ወደሌሎቹ አብያተ ክርስትያናት ስትልክ ከሌሎችም ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡትን እየተቀበለች ታስተናግዳለች በዚሕም ዓመት ቅዱስነታቸው ከስዊድንና ከአውስትርያ የመጡትን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ተወካዮችን በጥር ወር ተቀብለው ከማነጋገራቸውም በላይ ልዩ ልዩ ስጦታዎችን ሰጥተው አሰናብተዋቸዋል ።

ከዚሕም ሌላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ ኮሚሽን በየካቲት ወር በአደረገው ስብሰባ ለመገኘት መጥተው የነበሩትን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ልዑካን ተቀብለው አነጋግረዋል ።

ቅዱስነታቸው የትንሣኤን በዐል ምክንያት በማድረግ በበዐሉ ዋዜማ ለኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ስለክርስቶስ ትንሣኤ ሰፋ ያለ ቃለ ምዕዳን አስተላልፈዋል ።

በተለይ በዚህ ዓመት የመጀመሪያ የሆነው የመንበረ ፓትርያርክ አጠቃላይ የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተቋቁሟል ። ይህም ጉባኤ የ፲፬ቱ ሀገረ ስብከት አዲስ አበባና አሰብን ጨምሮ ሊቃነ ጳጳሳትና የሰበካ ጉባኤ አባላት መምሪያ ሐላፊዎችና ሊቃነ ካህናት ጥሪ የተደረገላቸው ዕንግዶች በተገኙበት በቅዱስ ፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ ዋና ጸሐፊነት ከግንቦት ፳፬ ቀን -፳፰ ቀን ፸፩ ዓ.ም. ታላቅ ስብሰባ ተደርጐ አባላቱን በመምረጥ አጠቃላይ የመንበረ ፓትርያርክ ሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤ ተቋቁሞአል ። ይህም ለቤተ ክርስቲያንዋና ለሰበካ ጉባኤ መጠናከር ከፍተኛ አስተዋፅዖ የበረከታል ተብሎ የታመነበት ስለሆነ ከዚህ የሚጠበቀው የሥራ ፍሬ ከሁሉ የላቀ ነው ።

በዚሁ ወር የቅዱስ ሲኖዶስ ስብሰባም በቅዱስ ፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት ተሰብስቦ በቤተ ክርስቲያንዋ በኩል ያለውን ችግር ተወያይቶ መፍትሔ ሰጥቶአል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር አባልነቷ ማኅበሩ በቨንኩቨር ካናዳ ለሚደረገው አጠቃላይ ቅድመ ዝግጅት በተደረገው ስብሰባ የጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ የተገኙበት ቡድን ወደ ናይሮቢ ሔዶ መልእክቱን ፈጽሞ ተመልሷል ።

የቅዱስ ፓትርያርኩ ፯ኛው ዓመት ሲመተ በዐል በዚሕ ዓመት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፸፩ ዓ.ም. በደማቅ አከባበር ተከብሮ ውሎአል በዚሕ ቀን ቅዱስነታቸው ለበዐሉ አከባበር ለተሰበሰበው ሕዝብ ቃለምእዳንና ቡራኬ ሰጥተዋል ።

ፍሥሐ ባንተ

# ዜና ሊቃውንት

## የአባ ወልደ ማርያም ቢሆነኝ አጭር የሕይወት ታሪክ

አባ ወ/ ማርያም ቢሆነኝ በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ልዩ ስሙ ቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ደብር በ፲፱፻፲፩ ዓ.ም. ግንቦት ፳፮ ቀን ከአባታቸው ከብላታ ቢሆነኝ የሱፌ ከእናታቸው ከወይዘሮ ብዙአየሁ ጐበዜ ተወለዱ ወላጆቻቸውም የዓለም ስማቸውን አሰፋ ብለው ሲያወጡላቸው የክርስትና ስማቸውን ደግሞ ወልደ ማርያም ብለው ሰየሙአቸው ፯ ዓመት ሲሆናቸው በዚያው በተወለዱበት ደብር ከታላቁ አባት ከአባ ወልደ ኢየሱስ ንባብና ዳዊት ከነመሪጌታ ክብረት ጋር ተማሩ ከዚያም የዲቁና ሙያቸውን እንዳጠናቀቁ የዲቁና ማዕርግ ተቀብለው እየቀደሱ ትምህርታቸውን ቀጥለው የቃል ትምህርትና ሰዓታተ ሊሊትንና መዓልትን ተምረው ቅዱስ ላሊበላ ደብር ከአባ ተክለ ማርያም ጋር ከመሪጌታ ጥበበ ቃል የቅኔ ትምህርት እንደጀመሩ በሕመም ምክንያት ለጥቂት ወራት አቋርጠውና አሳባቸውንም ለውጠው ወደመቄት ወረዳ ሔደው ገረገራ ጊዮርጊስ ከሚባለው ደብር ከመሪጌታ መንግሥቱ ጐሹ ጸዋትወ ዜማ ተምረው ወደ ተወለዱበት ደብር ተመልሰው ከመሪጌታ ካሣው አበበ ጾመ ድጓ ምዕራፍ አጠናቀው እንደተማሩ በሕግ ሚስት አግብተው የቅስና ማዕረግ በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም. ከአቡነ ጴጥሮስ ተቀበሉ በዚሁ ሥልጣናቸው ሲያገለግሉ ኢጣልያ ፋሽስት ወደ ኢትዮጵያ ምድር መጣ ሲባል አባ ወ/ማርያም የቅዱስ ነአኩቶ ለአብ ንዋየ ቅድሳት በጠላት እጅ እንዳይዘረፍ በልዩ ልዩ ምሥጢር የአሸተን ማርያምንም ንዋየ ቅድሳት ጭምር ሰውረው ለማዳን በቅተዋል ። በመጨረሻም ከክህነት ሚስታቸው ወ/ ገላየ የሚባሉ ሴት ልጅ ከወለዱ በኋላ ሚስታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩባቸው እርሳቸውም እስከ ሙት ዓመታቸው ድረስ በመቃብራቸው ቤት በጾም በጸሎት ተወስነው ከቆዩ በኋላ ከታላቁ አባት ከአባ ክፍሌ አየለ ዘንድ ቅኔ ሲማሩ ሳለ በፈቃደ እግዚአብሔር ከባሕታዊ ሀብተ ማርያም ጋር ሁነው ወደሸዋ ክፍለ ሀገር በእግር ተጉዘው ደብረ ሊባኖስ ገዳም ገቡ ከዚያም በገዳሙ ፭ ዓመት እንደረዱ በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም. በአባ ዘካርያስ ቆሞስ እጅ የምንኩስና ማዕርግ ተቀበሉ ድጋሜም ለ፭ ዓመት ያህል በገዳሙ እየረዱ አቋርጠው የነበሩትን የቅኔ ትምህርታቸውን ከየኔታ በኩረ ጽዮን ዘንድ ተምረው

እንደጨረሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጨረሻ ቦታቸው ተገልጾላቸው ከደብረሊባኖስ ወደ አዲስ አበባ መጥተው

ከዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ታዕካ ነገሥት በዓታ የካህናት ማሰልጠኛ በአዳሪ ትምህርት ቤት ገብተው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ዛሬ አቡነ ሚካኤል ከተባሉት የደብረ ዐባይ ቅዳሴን ተምረው እንደተመረቁ የመጻሕፍት ሐዲሳትን ትርጓሜ እማራለሁ ብለው እንደ ጀመሩ ስድስት ኪሎ አጠገብ በሚገኘው የካቲት 12 ሆስፒታል ውስጥ ዛሬ ምሳካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም የሚባለው ታቦት አዲስ ተተክሎ የመነኮሳት ገዳም ለማድረግ በሰፊው ታስቦ ስለነበር ከገዳሙ አባቴ ተክለ ማርያም ታዘው በ፲፱፻፴፱ ዓ.ም. አምጥተው ለገዳሙ አስተዳዳሪ ለነበሩት አቀረቡ አስተዳዳሪውም የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ቀዳሺ ሁነው በተጨማሪ የቅዳሴ መምህርና የሕፃናት መምህር ሁነው እንዲሠሩ ተቀጠሩ ከዚህ ዕለት ጀምረው ሰለቸኝ ደከመኝ ሳይሉ ለ





www.ethiopianorthodox.org

ዓመት ያህል እንዳገለገሉ በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም. በመናገሻ አውራጃ ለምትገኘው ገዳም ለሰበታ ማርያም መምህር ሁነው ተሾሙ በዚያም ፩ ዓመት ያህል እንዳገለገሉ ከማዘዝ ታዛዥ ሁኜ ብኖር ይሻለኛል ብለው ስለጠየቁ ተመልሰው እንደ ጥንቱ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም በማኅበራዊ ኑሮ ሁነው ቅዳሴአቸውን እየቀደሱ የቅዳሴ ትምህርታቸውን ያስተምሩ ጀመር ከዚያም ገበዝ ሁነው ብዙ ዘመን ካገለገሉ በኋላ በማኅበሩ ዘንድ ድካማቸው ተመዝኖ ማኅበራዊ ጸሎትን እያሳረጉ አዲስ ተቀጣሪ ዲያቆንና ቄስ መነኩሴ ሲመጣ የሥርዓተ ቅዳሴውንና የማኅበሩን ማለት የገዳሙን ደንብ አስጠኝና አለማማጅ ሁነው እንዲሠሩ ተመድበው እስከ ሕይወት ፍጻሜያቸው ድረስ በተአማኝነት አገልግለዋል ።

አባ ወ/ ማርያም ቢሆነኝ በዚህ ብቻ ሳይወሰኑ በትርፍ ጊዜአቸው የባሕር አሳብና የውዳሴ የቅዳሴ ማርያም ትርጓሜን ከአለቃ ወልደማርያም ዘንድ ከመማራቸውም በላይ የስብከትና የምዕመናንን መሳቢያ ዘዴ የሚያውቁ ስለነበሩ የብዙ ምእመናን አበ ንስሐ እየሆኑ ብዙ መንፈሳዊ ትሩፋትን ሠርተዋል ።

አባ ወ/ ማርያም ቢሆነኝ በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም በማኅበራዊ ኑሮ ሲኖሩ የተቸገረ ድኃ ሲያዩ ባላቸው አቅም የሚረዱበትን መንገድ እየፈለጉ ይረዱ ነበር ማደሪያ ላጣም መንገደኛ ከገዳሙ ውጭ በግል ገንዘባቸው ቤትን ሠርተው ልጃቸውን እንግዳ ተቀባይ አድርገው ይረዱ ነበር አባ ወ/ ማርያም ቢሆነኝ በእንደበታቸው ሽንገላና ውሸት የማይወጣቸው የመጨረሻ ሐቀኛ ሰው ነበሩ የምዕመናንም ንስሐ አባት በነበሩበት ጊዜ በኑዛዜ ጊዜ በተአማኝነት የሚገኙ ፍጹም ንጹሕ መነኩሴ ነበሩ የአዳም ልጅ እንደመሆናቸው በምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም ገዳም ፴፯ ዓመት ከዚያ በፊት ፴፱ ዓመት በትምህርት በሀገር ቤት በገዳም ከኖሩ በኋላ በ፸፭ ዓመታቸው በ፲፱፻፸፭ ዓ.ም. ሰኔ ፲፰ ቀን በመኪና አደጋ አርፈው በቀጨኔ መድኃኔ ዓለም ሰኔ ፲፱ ቀን ብዙ ምዕመናን በተገኙበት በክብር በሥነ ሥርዓት ቀብራቸው ተፈጽሟል ።

ከመቃብራቸውም ላይ ወ/ተ ኮላች አርአያ የተባሉ የንስሐ ልጃቸው የአባ ወ/ ማርያምን መንፈሳዊ ስራቸውን ለመግለጽ ሐውልት አሠርተውላቸዋል ። የምስካየ ኅዙናን መድኃኔ ዓለም የሰበካ ጉባዔ ጽ/ ቤትም ለቀብራቸው ሥነ ሥርዓት ማስፈጸሚያ ልዩ ወጪ አድርገውላቸዋል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንም መንፈሳዊ ዜናቸውን እየገለጸች ነፍሳቸው ዕረፍተ ነፍስ እንድታገኝ በጸሎት ታስባቸዋለች ።

የዜናው አቅራቢ.
አ/ገብረ መስቀል ተስፋዬ ዘገነተ ማርያም

# የፍጡርን ችግር በፍጡር

የቅዱሳን መላእክት አገልግሎት እጅግ ከፍተኛ በመሆኑ በዚህ አጭር ታሪክ ማጠቃለል አይቻልም ። በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ የፈለግሁት የቅዱስ ሩፋኤልን ተራዳኢነትና የጦቢትን ስለሆነ ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ለማቅረብ እሞክራለሁ ።

በመሠረቱ ሩፋኤል ማለት የአምላክ ደስታ ፤ ልቡናን ደስ የሚያሰኝ ማለት ነው ። ቅዱስ ሩፋኤል ለሰዎች ብቻ ሳይሆን ለእንስሳት ጭምር ከፍተኛ አገልግሎት የሚፈጽም ሲሆን በሲመተ መላእክት ደረጃም ቅዱስ ሩፋኤል ፫ኛ ማዕረግ አለው ። በማዕረግ ፩ኛ ቅዱስ ሚካኤል ፪ኛ/ ቅዱስ ገብርኤል ሲሆኑ ቅዱስ ሩፋኤል ፫ኛ ነው ። ቅዱስ ሩፋኤል በመልካም አድራጐት የሰው ልጆችን እንዲያገለግል ከኃያሉ እግዚአብሔር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ጦቢትን እና ልጁን ጦቢያን እንዲሁም ሣራ ወለተ ራጉኤልን ከደረሰባቸው ከፍተኛ ችግር ሁሉ ረድቶአቸዋል ።

ጦቢት ስደተኛ ሆኖ በፋርስ የሚኖር ጻድቅ ሰው ነበር ። ይህ ሰው በወገኖቹ መማረክና በእርሱ ላይ በሚፈጽመው ግፍ በጣም ያዝንና ያለቅስ ነበር ። ኃዘኑም ስለበረታ ቅዱስ ሩፋኤል በየጊዜው በአምሳለ ብዕሲ እየተገለጠ ይረዳውና ያጽናናው ጀመር ።

ስለዚህ ጦቢት ቀደም ሲል ያስቀመጠውን ገንዘብ ልጁ ጦብያ እንዲያመጣለት እየተመኘ ሳለ ልጁ ብቸኛ ስለሆነ ከዕለታት አንድ ቀን ሩፋኤል በሰው ተመስሎ ለጦቢያ ተገለጸለትና የአባቱን ገንዘብ ለማምጣት በሄደበት ጊዜ እንደሚረዳው ስለነገረው በነገሩ ተስማምቶ ወደ አባቱ ወሰደው ። አባትየውም ልጁን አደራ ብሎት እንደሰው ሁኖ የቀረበው ታዳጊ መልአኩና ጦቢያ ሖንገዳቸውን ቀጠሉ ሲሔዱ ውለው ማታ ጤግሮስ ከሚባለው ወንዝ ደረሱ። ከወንዙም ጦብያ ዕግሩን ሲታጠብ ታላቅ ዓሣ ከባህሩ ውስጥ ወደጦብያ በመጣ ጊዜ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦብያን ዓሣውን ያዘው ። አይዞህ አትፍራው ልቡን ፤ ሆዱንና ሀሞቱን አውጥተህ ያዘው አለው ።

እርሱም መልአኩ እንዳዘዘው አደረገ ። ከዚያ በኋላ መልአኩና ጦብያ ከራጉኤል ቤት በደረሱ ጊዜ ሣራ እና እናቱ በደስታ ተቀበሏቸው ። ጦብያ ግን የሣራን ቁንጅና የደሟንም ደም ግባት ስለወደደ እርሷን አግብቶ ለመመለስ በልቡ ወሰነ ። ሀሳቡንም ገልጦ ለአባቷ ስለ ነገረው አባቱዋ በልጁ ላይ ያለበትን አሳዛኝ ሁኔታ ግልጥልጥ አድርጐ ለጋብቻ እንደማትሆነው አስረዳው ።

ሁኔታውን እንዲህ ሲል ገለጸለት ፤ እነሆ ልጅዋን ለ፯ ባሎች ዳርኳት ፤ዳሩ ግን ስድስቱም ስለሞቱባት እነሆ ያለባል ትገኛለች ። ስለዚህ አንተም ብታገባት ሰባተኛውን ገደለች እየተባለ ያገር መሣቅያ ከምትሆን ቢቀርባት ይሻላል አለው ።ጦብያ ግን እግዚአብሔር ሁሉንም ማድረግ የሚችል አምላክ በመሆኑ እግዚአብሔር እኔንም ያድነኛልና በዚህ አትጨነቅ ወድጃታለሁና አገባታለሁ አለው ።

በዚሁ ሁኔታ ፈጸመና መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል እንደነገረው የዓሣውን ልብና ሀሞት ሲያጤሰው አስማንድያስ የሚባለው በሣራ አድሮ ባሎቹዋን ይገድል የነበረው ጋኔን በኖ ጠፋ ፤ አባቱዋ ግን እንደተለመደው ሰባተኛው ባል ጥዋት ሞቶ አገኘዋለሁ ብሎ በሥጋት አድሮ ሲነጋ ቢያይ በሕይወት በማደሩ ተደነቀ ። ከዚያ በኋላ በአደራ የተቀመጠውን የአባቱን ገንዘብ ገባኤል ዘንድ ይዞ ያላሰባትንም ቆንጆ ሚስት አግብቶ ወደ አባቱ ተመለሰ ። በአማቾቹ ቤት ፴ ቀን በሙሽርነት ቆይተው ስለነበረ ወላጆቹ በከባድ ጭንቅ ላይ ሳሉ ያልታሰበች ሚስት አግብቶ በሰላም በመመለሱ እጅግ ተደሰቱ ። ጦብያም ከመልአኩ ከቅዱስ ሩፋኤል በተነገረው አማናዊ ቃል መሠረት የዓሣውን ሀሞት አሣርሮ የአባቱን ዓይን ቢኩለው ዓይኑ ወዲያውኑ በራ ።

የእግዚአብሔር ረድኤት ካልተለየ ቅዱሳንመላእክትእንዲህዓይነትአገልግሎትያበረክታሉ።ቅዱስሩፋኤልያበረከተውን ቅን አገልግሎት ስንመለከት፩ኛ/ ብዙ ባሎች እንዲሞቱባት ያደረገውን አስማንድዮስ የተባለ ጋኔን አስወጣው ።፪ኛ/ በችግር የተቆራመደው ጦቢት በአደራ ያስቀመጠውን ገንዘብ አግኝቶ ከችግሩ እንዲገላገል ረዳው ። ፫ኛ/የታወረውን የጦቢትን ዓይን አብርቶ በእውርነት ከመኖር ገላገለው ። ቅዱሳን መላእክት ዛሬም ለሚያምንባቸው ከዚህም የበለጠ ርዳታ ያደርጋሉ እያደረጉም ናቸው ።

ዳሩ ግን ሰዎች በችግራቸው ጊዜ የተደረገላቸውን መልካም ነገር ሁሉ በመዘንጋት ሰውም ሆነ እግዚአብሔር ያደረገላቸውን ሁሉ ከንቱ ያደርጉታል ።

በዚህም ብቻም አይወሰኑም እግዚአብሔር ያደረገላቸውን መልካም ነገርም ሠውረው በራሳቸው ኃይልና ሥልጣን ያደረጉት ለመምሰል ጥረት ያደርጋሉ ። ዳሩ ግን ራስን አለማወቅና ጻድቅ አድርጐ ማቅረብም ሌላው ኃጢአት ነውና ጉዳቱ ያመዝናል ።

የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ዙሪያ ነው እንደተባለው መላእክት በተራዳኢነታቸው የሚያምኑባቸውን ይረዳሉ ፤ ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ሥልጣን በማይቀበሉም ተግሣጻቸውን ያስተላልፋሉ ።

ስለዚህ መላእክት በእግዚአብሔርፊት የሚቆሙ የእግዚአብሔርንም ቅዱስ ፈቃድና ምህረት የሚያስተላልፉ መሆናቸውን አምነን ከእግዚአብሔር በሚተላለፈው ምህረት ለመጠቀም እንሞክር ።

ተስፋ ጥሩነህ

# የግብርና በረከት

የተሻሻሉ ዓመታዊ የእንስሳት መኖ

ዕዳት የከብት (ድንች ፎደር ቢት)

የከብት ድንች የመጀመሪያ ሙከራ በአርሲ ገጠር ልማት ድርጅት በ፲፱፻፷፩ ዓ.ም. በቁልምሳ የእርሻ ምርምር ጣቢያ ተጀመረ ። በዚህ ወቅት ከስዊድን አገር ሁለት የከብት ድንች ዓይነቶች በማምጣት የዓይነት ሙከራ ተከናውኖ ከ፰ - ፲ ቶንስ በሄክታር ምርት ተገኘ ።

የከብት ድንች ምርምርን በማስፋፋት በዛ ያሉ የዘር ዓይነትን ከውጭ በማስመጣት የዓይነት ሙከራ ለተለያዩ ዓመታት ተከናውነው የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል ። (ሠንጠረዥ)

ሠንጠረዥ ፩
የከብት ድንች ዓይነት ሙከራ

| ዓይነት | ምርት (ኪሎ በሄክታር) |
| --- | --- |
| አሪንግ ቤሪስ /ስዊድን | 15800 |
| ፖጅ በሬክስ | 14890 |
| ቤሪስ ሃልቫንግ | 14450 |
| ሬድ ኦቱፍቴ | 14380 |
| አሪንግ ቤሪስ /ኢትዮጵያ | 13830 |
| ኖቫ | 12860 |

በዚህ ውጤት አሪንግ ቤሪስ ከፍተኛ ምርትን ያስገኘ እንደመሆኑ መጠን ሌላ ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደ የዘር ወቅት ጥናት ቀጥሎ የሚከተለው ውጤት ተገኝቶአል

ሠንጠረዥ ፪
## የከብት ድንች ዓይነት መከራ

| የዘር ወቅት (በወር | ምርት (ኪሎ በሄክታር |
| --- | --- |
| መጋቢት | 30.420 |
| ሰኔ | 18.300 |
| ሐምሌ | 7.200 |

ሠንጠረዥ ፪ እንደሚያመለክተው ከፍተኛ ምርት በመጋቢት የተዘራው ሲያሳይ በሰኔ የተዘራ ምርት 40% በሐምሌ የተዘራው 76 % እንደሚቀንስ የከብት ድንች ብዙ ንጥረ ነገሮችን ምስረታና ግንባታ እንዲሁም ለቅጠል ዕድገት ስለሚያስፈልገው የፎስፎረስና የናይትሮጂን መጠን ጥናት ተካሂዶ በተገኘው ጥናት መሠረት ከፍተኛ ፎስፎረስና (138 ኪሎ በሄክታር) መሐከለኛ ናይቶጅን (46 ኪሎ በሄክታር) ምርትን ከፍ እንደሚያደርግ ተደርሶበታል ። ይኸን የከብት ድንች በአርሶ አደሩ አካባቢ ለማስተዋወቅ በአርሲ ክ/ ሀገር በምርጥ ገበሬዎች አካባቢ በእርሻ ወኪሎች አማካይነት ዘር በመስጠትና ስለዚሁም የከብት ድንች አመራረትና አጠቃቀም ቅስቀሳ በማድረግ ለማስተዋወቁ ሥራ ተጀመረ ። በመጀመሪያ ጊዜ ብዙ ችግሮችም ቢኖሩም ከጊዜ በኋላ አርሶ አደሩ ይኸን የከብት ድንች በአነስተኛ ቦታ በተለይም ለመጀመሪያ ጊዜ እንደ ጓሮ አትክልት )ከፍተኛ ምርትን በማግኘቱና በወተት ላሞቹን በእርሻ በሬዎቹም ተወዳጅነት ስለአገኘ ዛሬ የአርሲ

ወደ ገጽ ፤ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተሰብዕ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

## ቅዱስ ጋብቻ

**"ጋብቻ የሁሉም እናት ናት"**

በማንኛውም የዓለም ኅብረተሰብእ ውስጥ እያንዳንዱ መንግሥት ወይም ሕዝብ የብዙ ቤተሰብእ ድምር ውጤት ነው ።

ስለዚህ ጋብቻ የሁሉ እናት ብትባል ወይም ከዚህ በከበረ ቃል ቢነገርላት ሐሰት አይሆንም በየጊዜው እየተነሱ ያለፉ ሊቃውንትም ባላቸው የእውቀት መጠን ያህል በተለያየ አነጋገር ገልፀ

ውለታል ። ጋብቻ የሁሉም እናት ናት'' የሚለውም ይትባሀል ከሊቃውንት የተ ገኘ ነው ። በመሆኑም የዓለም ሕዝቦች በሙሉ ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት የሚለውን የእግዚአብሔር ሕግ ሲፈጽሙት ይኖራሉ ። በዚህም መሠረት ዓለማችን በብዙ ሕዝቦች ተመልታ ትገኛለች ይህም ትዕዛዝና ሕግ እስከ ህልፈተ ዓለም ድረስ የሚቀጥል ሆኖ የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እየፈፀመ የተፈጥሮ ሕግ ሆኖ ሲከበር ይኖራል ማለት ነው።

ዓለምን በጥበቡ የፈጠረ እግዚአብሔር አምላክ ጋብቻንም በጥበብ ፈጥሮታል ይኸውም ሌላ መፍጠር ሳይሳነው ወይም ከሌላ ማስገኘት ከአዳም የጐን አጥንትበመንሣት(በማውጣት)ሔዋንን አስገኝቷል ። ለአዳም ሔዋን ብቻ ለሔዋን አዳም ብቻ መሆኑን ለማሳወቅ ነው ። እንዲህ ዓይነቱም ጋብቻ ፤

- ብዙ ተባዙ ምድርንም ምሉአት
- ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ በሚል ኃይለ ቃል አድንቆታል ።

ከቅዱስ መጽሐፋችን ስለጋብቻ በብዙ ቦታ ተጽፏል ከነዚህም ውስጥ ዋና ሆኖ ሊገለጽ የሚገባው አሁንም የጌታችን በሠርግ ቤት ተገኝቶ ውሃውን ወደ ወይን ጠጅ በመለወጥ የፈፀመው የመጀመሪያ ተአምር የጋብቻን ክቡርነትና ታላቅነት ለመግለጽ መሆኑ ጉልህ ማስረጃ ነው ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችንም ካሏት ሰባት ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ጋብቻ ነው ይህም በቤተ ክርስቲያናችን አጠራር ምሥጢረ ተክሊል ይባላል ይህንንም በትምህርቱ ሁሉ አስፍታ ገልጣ ለምዕመናን ታስተምራለች ለሚቀርቡትም ተጋቢዎች ትፈጽምላቸዋለች በዚህም ሁኔታ የተመሠረተ ጋብቻ ቅዱስ ከመሆኑም ሌላ ሁለቱን ወጣቶች ወይም ተጋቢዎች ወደ አንድ ቤተሰብነት የመለወጥ ኃይል ያለው ስለሆነ ምሥጢር ይባላል ።

በዚሁም መሠረት የቤተ ክርስቲያናችንን ሕግና ሥርዓት በመከተል ወጣት ዓለሙ ቀልቤሳና ወ/ት እትዩ ፀጋዬ ጥር ፳፱ ቀን ፲፱፻፹፭ ዓ.ም. በደብረ አሚን ተክለ ሃይማኖት ቤ/ክ ቅዱስ ጋብቻቸውን በተክሊልና በሥጋው ደሙ ፈጽመዋል ። እነዚህ ሁለት ወጣቶች ለአቅመ አዳምና ለአቅመ ሔዋን ከመድረሳቸው በፊት በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርትና ሥርዓት ታንፀው ያደጉ ከመሆናቸውም በላይ በአሁኑም ጊዜ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በመሳተፍ አገልግሎት ያበረከቱና የሚያበረክቱም ናቸው ።

ወጣት ዓለሙ ቀልቤሳ ቀደም ሲል በምክሀ ደናግል ማርያም የሰንበት ት/ቤት በአባልነትና በልዩ ልዩ መንፈሳዊ አገልግሎት ብዙ ድርሻ ያበረከተ ሲሆን በአሁኑ ጊዜም በማኅበሩ አማካይኝነት እየተዘጋጀ በሚቀርበው የስብከተ ወንጌል ፕሮግራም የትምህርት ክፍል ኃላፊ በመሆን የሚያገለግል ነው ወ/ት እትዩ ፀጋዬም ባላት መንፈሳዊ አገልግሎትና ትጋት ከእርሱ ተለይታ የማትታይ ናት በመሆኑም ሁለቱ ወጣቶች ባላቸው መንፈሳዊ ሕይወት የመሠረቱት ይህ ቅዱስ ጋብቻ ፍሬውምመልካም እንደሚሆን አያጠራጥርም ።

ከቦታው ድረስ ተገኝተን ያፈጸጸሙን ሁኔታ እንደተመለከትነውም ጋብቻቸውን እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት ለፈፀሙት ሁለት ወጣቶች በሰበካው የሚኖሩምዕመናንከየአድባራቱምየመጡየሰንበትት/ቤትአባላት፣ጥሪየተደረገላቸው እንግዶችና የምክሃ ደናግል ማርያም የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ደማቅ የሆነ አቀባበልና አሸኛኘት አድርገውላቸዋል ። በተለይም የምክሀ ድናግል ማርያም የሰንበት ት/ቤት ተማሪዎች ለሙሽሮቹ መልካም ጋብቻቸውን ማብሰሪያ ይሆን ዘንድ እቅፍ አበባ አበርክተውላቸዋል ።

ከዚህም በኋላ ልዩ ልዩ መወድስ ቅኔ ተበርክቶላቸው እንዳበቃ የዕለቱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋብቻን በሚመለከት ሁኔታ ሰፋ ብሎ ከተሰጠ በኋላ የደብሩ አስተዳዳሪ መምህር ዘካሪያስ አሳርገውላቸዋል ።

በመጨረሻም በምክሃ ደናግል ማርያም የሰንበት ት/ቤት አዳራሽ ለሙሽሮቹና ለታደሙት እንግዶች የቁርስና የሻይ ግብዣ ሰፋ ባለ ሁኔታ ተደርጎላቸው ወደ ቀኑ ፕሮግራም በማምራት የጧቱ ፕሮግራም ተፈጽሟል ።

ለሚከተለው ይህ ዓይነት ክብር የመልካም ኑሮ መርህ ነው የሚኖረውም ደረጃ በጋብቻ ውስጥ ሆነው ኑሮአቸውን በመግፋት ዛሬም ከቅዱሳን ጋር እንደሚጠሩት እንደአብርሃምና ሣራ እንደነ ይስሐቅና ርብቃ ከሌሎቹም ቅዱሳን ሁሉ ሊመሳሰል ይችላል ።

የሙሽሮቹም ኑሮ በዚህ ዓይነት እንዲሆን መልካም ምኞታችን ነው ።



# የጤና አምድ

## የሳምባ ነቀርሳ በሽታ

"እነሆ እግዚአብሔር ኃያል ነው ፤ ማንንም አይንቅም" መጽሐፈ ኢዮብ ም. ፴፮ ፡ ፭

ስለ ሣንባ ጥቅም ሰንባ ከሰውነታችን ትላልቅ ክፍሎች አንዱ ሲሆን የሚገኘውም በጐደን አጥንታችን ተሸፍኖ በደረታችን ውስጥ የሚገኝ የመተንፈሻ አካል ነው የሣንባ የግራ ክፍል ሁለት ክፍሎች አሉት የቀኙ የሣምባ ክፍል ደግሞ በሦስት ተከፍሏል ። ሣምባ የሚያገለግለው ንፁሕ አየርን ከውጭ ወደ ውስጥ በማስገባት የተ ቃጠለውን አየር ከውስጥ ወደ ውጭ ለማስወጣት ነው ።

ሣምባን ብዙ ነገሮች ሊያጠቁት ሲችሉ ብዙውን ጊዜ በአየር ላይ የሚገኙ ጥቃቅን ህዋሳት ወደ ሳምባ ሊገቡ ይችላሉ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የሳምባ ነቀርሳ በሽታ ነው ። ይህንን በሽታ ሊያመጡት ከሚችሉት ጥቃቅን ህዋሳት ውስጥ አንዱ ባክቴሪያ ነው ይህ ባክቴሪያ ከአየር ጋር በመቀላቀል ወደ ውስጥ በምናስገባው አየር አማካይነት ሊገባ ይችላል ከዚያም በሣምባችን ውስጥ በመራባት የሳምባን ክፍሎች ይጐዳል ። ሁለተኛው የሳምባ ነቀርሳ በሽታ መነሻ ደግሞ በዚህ በሽታ ከተበከሉ እንስሶች የምናገኘውን ወተት ሣናፈላ በመጠጣት በቀላሉ ሊይዘን ይችላል ።

፫ኛው የበሽታው መነሻ ደግሞ በዚህ በሽታ የተበከሉትን ሰዎች በመቅረብ በሚተነፍሱበት ፡ በሚስሉበት ፡ በሚያስነጥሱበት ጊዜ አጠገባቸው በመሆን በቀላሉ በትንፋሽ ሊተላለፍ ሲችል በተጨማሪም እነዚህ ሰዎች በሚጠቀሙበት ዕቃ ለምሳሌ በመጠጫ ዕቃዎቻቸው በምግብ መብያቸው በመጠቀም ይህ በሽታ በቀላሉ ሊተላለፍ ይችላል።

ይህ በሽታ በሚጀምርበት ጊዜ የሚያሳያቸው ምልክቶች አሉ ። እነዚህም የመተንፈሻ አካሎችን እንዲሁም የሳምባ ያላይኛውን ክፍል ጭምር ይይዛል ማለት ነው ። ሌላው ደግሞ በጉሮሮ አካባቢ የሚገኙትን እጢዎች እና ጉሮሮ ጭምር እነዚህ ባክተሪያዎች ሊጐዱ ይችላሉ ።

እነዚህ ባክተሪያዎችም ደም ውስጥ በመግባት የሰውነትን ህዋሳት ይበክላሉ በተለይም ባክተሪያዎች በሳምባ ክፍል በመግባት ከተሰበሰቡ በኋላ ሳምባን ያቆስሉታል ከዚህም የተነሣ በሣምባ ላይ ፈሳሽ ነገሮችን ወይም ደግሞ አክታን የፈጠረው ሌላው ደግሞ በሰውነቱ ላይ የሚሰማው ህመም ወይም ምልክቶች ይኖሩታል ። ከነዚህም ውስጥ የሰውነት ክብደት መቀነስ ሃይለኛ ደረቅ ሣል ፤ ሌላው ደግሞ ህመምተኛው ካለምንም ሥራ ይደክመዋል ። በተለይም ጊዜ በመለየት ከቀትር በኋላ ሲሆን ድካም ይሰማል ። ይህ በሽታ እየጠነከረ በሚሔድበት ጊዜ ህመምተኛው የተለያዩ ሁኔታዎች ይሰማዋል በተለይም ምግብ ከተበላ በኋላ የሆድ ህመም እና የሚያስመልስ ሁኔታ ይታይበታል ሣሉም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመሔድ ለአንድ ሣምንት ያህል ብዙ አክታ ያስለዋል ከዚህ በኋላ ደም መቀላቀል የደም አክታን ያመጣል አክታው የበዛ ይሆናል ።

ነገር ግን ከፍተኛው ችግር በበሽታው የተበከለው ደም ከሳምባ ክፍሎች ወደ ጤናማው የሳምባ ክፍል የሄደ እንደሆነ ነው በዚህ ሁኔታ ላይ ህመምተኛው የደም ግፊት ያነሰ ይሆናል ይኸውም የደም ማነስ ይይዘዋል ።

ይህ በሽታ ሊታወቅ የሚችለው በሽተኛው በሚያሳየው ምልክትና አክታን በመመርመር እንዲሁም ራጅ በማንሣት ነው ።

የዚህ በሽታ ህክምናው ፩/ ይህ በሽታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ ህመምተኛው በሆስፒታል ውስጥ በመተኛት መታከም አለበት ህመምተኛው የደም ማነስ ስላለው ደም ይሰጠዋል ።

፪/ ሌላው ደግሞ ለሳምባ በሽታ የሚታዘዘው ህክምና ለረጅም ጊዜ የሚወስድ ስለሆነ ህመምተኛው ባለመሰልቸት በትክክል መድኃኒቱን መጠቀም አለበት አለበለዚያ ግን ህመምተኛው ከህመሙ ሊድን አይችልም ፤

፫/ በዚህ በሽታ ምክንያት ህመምተኛው የአእምሮ ጭንቀት ስላለበት በከፍተኛ ሁኔታ ማጽናናት አስፈላጊ ነው።

፬/ ህመምተኛው የተመጣጠነ ምግቦችን መመገብ ያስፈልገዋል ለምሳሌ ያህል በፕሮቲን በባይታሚንና ኃይል ሰጪ የሆኑ ምግቦች ያስፈልጉታል ምክንያቱምየህመምተኛውሰውነትበሽታውን መቋቋም እንዲችል እና በቀላሉ ለመዳንም እንዲረዳው ነው ።

፭/ ህመምተኛው ይህ በሽታ እንደያዘው ከታወቀ የሚጠቀምባቸው ዕቃዎች ማለትም መጠጫዎችንና ምግብ መመገቢያዎችን ለይቶ ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው ።

፮/ ይህ በሽታ በቀላሉ በትንፋሽ ከህመምተኛው ወደ ጤነኛው ሰው ስለሚተላለፍ ህመምተኛው በሚስልበት በሚያስነጥስበትና በሚተነፍስበት ጊዜ አፉን በመሐረብ ማፈን ያስፈልገዋል ።

፯/ ሌላው ደግሞ ሕመምተኛው በሚስልበት ጊዜ የሚወጣውን አክታ መሬት ላይ ከመትፋት ይልቅ በተወሰነ ዕቃ ውስጥ በማጠራቀም ማቃጠል ያስፈልጋል ።

፰/ ህመምተኛው በሆስፒታል ውስጥ እየታከመ ሣለ ህመሙ እስኪታገሥ



www.ethiopianorthodox.org

ለት ድረስ በተለይም አክታው ተመርምሮ ከባክተሪያ ነፃ እስከሆነ ድረስ በተለይ ክፍል ተገልሎ ለብቻው መታከም አለበት ።

፱/ ህመምተኛው ከዳነ በኋላ በሽታውን ሊቀሰቅሱ የሚችሉትን ነገሮች ማድረግ የለበትም ለምሳሌ አልኮል መጠጣት እንዲሁም ለአቧራ መጋለጥ አያስፈልገውም ማለት ነው ።

የሳንባ ነቀርሣ በሽታ መከላከያ ፩/ ዋነኛውና በጣም አስፈላጊ ከሆኑት መከላከያዎች ውስጥ አንዱ ክትባት ነው።

ክትባት የሚጠቅመው በበሽታው ለተያዘው ሰው ሳይሆን ከዚህ በፊት ህመሙ ለማያውቀው ነው ህፃናት ሰውነታቸው በሽታን የመቋቋም ኃይሉ አነስተኛ ስለሆነ ይህ በሽታ በቀላል ሊያጠቃቸው ይችላል ። ስለዚህ በልጅነታቸው የሳምባ ነቀርሣ በሽታ መከላከያ የሆነውን ክትባት መከተብ አለባቸው ።

፪ ሌላው መከላከያ ደግሞ የንፅህና አጠባበቅ ነው ። ይኸውም ከቤት ውስጥና በአካባቢ የሚገኙትን ቆሻሻዎች ማቃጠልና በአጠቃላይ የምግብ መመገቢያዎችን እና የመጠጫ ዕቃዎችን ሁሉ በንፅህና በመያዝ ከበሽታው ለመራቅ ይቻላል ።

ተማሪ ነርስ መንበረ ምህረቱ

## ዘመን ካልሠሩበት ፤

በዘመን መሥራት እንጂ ዘመንን ቢቆጥሩት በየዓመቱ እያለዋወጡ አዲስ ዘመን ቢሉት ያለፈውንም አሮጌ ስም ቢሰጡት ካልሠሩበት ድኅነት እንጂ ብልጽግና አይገኝለትም ።

ዘመን አሮጌ የሚሆነው ተግቶ ላልሠራበትና ተኝቶ ላሳለፈው መንፈሰ ደካማ ከሆነው በቀር ለሚሠራበት ሰው ቢያልፍም በረከትንና የማያልቅ የመንፈስ ብርታትን አጐናጽፎት ስለሚለወጥ በሠራተኛ በኩል አሮጌ የሚለው ስም የሠራበት መሆኑን ይገልጻል ።

የማይሠራ ግን አዲሱም ዘመን ቢሆን ስለማይሠራበት ያው ተመልሶ አሮጌ ሆኖበት ያልፋል ይህ ሁኔታ ሊደርስ የሚችለው አንዳንድ ሰዎች ዝና ወዳድ በመሆናቸው ዘመን መቁጠር እንጂ በዘመን ሠርቶ ለመጠቀም ልምድ ስለሌላቸው አሮጌውን ሲሸኙ አዲሱን ሲቀበሉ የሥራ ለውጥ ሳያዩና ሳያሳዩ የዘመንን ለውጥ ብቻ እየተከታተሉ ይኖራሉ ።

ታዲያ እንደነዚህ ያሉ ሰዎች የሚጠቅመውን ሳያውቁ በሆነ ባልሆነው አሳባቸውን በየጊዜው እያለዋወጡ የዘመን መፈራረቂያ ብቻ ሆነውይቀራሉ ነገር ግን በየዕለቱ ራሳቸውን በየጊዜው በሚያሻሽሉ ብልሆች ዘንድ እንኳን ዓመት ዕለትም ለአዲስ የሥራ ክንውን ይናፍቃቸዋል ።

አንዳንድ ብልሆች ሰዎች እህል በቁናጡ ወርቅ በሚዛን መንገድ በኪሎ ሜትር እንደሚለካና እንደሚሠፈር የፍጡራን ዕድሜ መለኪያው ዘመን መሆኑን ስለሚያውቁ ዕድሜያቸውም ይነስ ይብዛ ለሥራ የሚያበቃ ዕድሜ ካገኙ በጊዜ ያቸው ሣይሠሩበት ለማለፍ አይፈልጉም ።

በተለይ የዕውቀት ጮራ በመላው ዓለም በተዳረሰበት በአሁኑ ጊዜ ሰዎች የራሳቸውን ለሌሎች የሌሎችንም ለራሳቸው ለማትረፍ አስፈላጊ መሆኑን ስለሚያምኑበትሣይሠሩ በብቸኝነት መጋረጃ ውስጥ ለመቀመጥ የሚፈልጉ ቢኖሩ በዓለም ያልታየና ያልታወቀ ነገር ሲመጣ አዲስ ነው ሊባል ይችላል ። አዲስ ማለትም በፊት ያልነበረና አሁን ግና ያልተለየ ማለት ነው ። ግን ዘመናት የሚፈራረቁ እንጂ አዲስ ሊሆኑ አይችሉም ስለዚህም ሰውም ሆነ ጊዜ ያረጀው ሳያልፍ አዲስ ይተካል የተተካውም አዲስ ተብሎ ይጠራል ።

በክርስትና ሕይወት ግን እንዲህ አይደለም ያረጀው ይታደሳል አሮጌው አዲስ ይሆናል ምክንያቱም በዘመኑ ሳይሆን የሚታደሰው በሚሠራው መልካም ሥራ ነውና ነው ።

ታዲያ ይህ አዲስ ሕይወት በክርስቶስ በማመን የሚገኝ የልብ ተሐድሶ እንጂ በስንፍና ተውጠው ዘመኑን ብቻ ለሚቆጥሩ ሰነፎች ሰዎች አይደለም ።

አንዳንድ አስተዋይ ሰዎች አዲስ ዓመት በመጣ ቁጥር የቀደመ ተግባራቸውን ይገመግማሉ ያለፈ ሕይወታቸውን ይመረምራሉ በማይገባ ሁኔታ አሳልፈው ከሆነ ከስሕተታቸው ይማራሉ የፈጸሙት ጠቃሚ ተግባርም ካለ የበለጠ ለመሥራት ዕቅድ ያወጣሉ ።

በዚሁ አንፃር ክርስቶስን የተቀበለ ክርስቲያንም ራሱን የሚመረምርበትና የሚፈትንበት ጊዜ ሊኖረው ይገባል ፪ ቆሮ ፲፫ ፡፭ .

እንዲያውም ከዓለም ሳይሆን በዓለም የሚኖር አንድ ፈላስፋ ነበር ይባላል ይህን ፈላስፋ በብቸኝነትና ያለ ሥራ ዘመኑን እንዴት ትገፋዋለህ? ቢሉት "እኔ እኮ ብቻዬንና ያለሥራ ዘመኔን የምሸኝ አይደለሁም ከሚመክሩኝና ከሚያሠሩኝ ከሚያጫውቱኝና ከሚያወያዩኝ ከብዙ ሰዎች ጋር ነው ያለሁ አለና ከጐኑ መጻሕፍትን አወጣና ይህ አብሮኝ የሚኖረውና የሚያወያየኝ ጋሊኖስ ነው ። ይህም የሚመክረኝ አብቅ

ወደ ገጽ ፳፪ ዞሯል



## ለፍርድ ትቀርባለህና ተዘጋጅ

እንዳድ አእምሮ ቢስና የማያስተውል ሰው በሰው ላይ መፍረድ ቀላል ነገር መስሎ ይታየው ይሆናል ። አስተዋዮችና ፈሪሃ እግዚአብሔር ያደረባቸው ሰዎች ግን በሰው ከመፍረድ ይልቅ በራሳቸው ላይ ቢፈረድባቸው ይመርጣሉ ። "እንዳይፈረድባችሁ አትፍረዱ ፡በምትፈርዱበት ፍርድ ይፈረድባችኋል " የሚለውን አምላካዊ ቃል ጠንቅቀው ያውቃሉና ።

በመሠረቱ በርእሰ ትምህርቱ ላይ የሠፈረው ኃይለ ቃል የሚያስደነግጥ ነው ብቻ በዓለም ላይ ያለው የአዳም ልጅ ሁሉ በሚያሳልፈው ውሱን ዘመኑ እርስ በእርስ ያልተካሰሰ ወይም ያልተከሰሰ ስለማይገኝ ይፈረድብሃል ቢሉት እንኳ ለምዱታልና እምብዛም አይደነግጥም ይሆናል ።

አልፎ አልፎም ተከሳሹ ከሳሽ ከሳሹ ተከሳሽ የሚሆንበት ጊዜ ስላለ" ለፍርድ ትቀርባለህና ተዘጋጅ" የሚለው ቃል በማን ለማን እንደሚፈረድ ስለማያውቅ ወይም አስተውሎ ስለማይመረምር ደንታ ሊኖረው አይችልም ።በሌላም አመለካከት ሁለት ሰዎች ከሳሽና ተከሳሽ ሆነው ፍ/ቤት ከቀረቡ በኋላ ይፈርድለታል የተባለው ሲፈረድበት ፡ይፈረድበታል ተብሎ የተጠበቀው ሲፈረድለት ያየ ወይም የሰማ ደግሞ ስለ ፍርድ ጉዳይ መቅለልና መክበድ መገምገም አይችልም ። የፍርድ አዟዟር ግን"ከአያያዝ ይቀደዳል ከአነጋገር ይፈረዳል" ተብሎ እንደተተረተው ጉዳዩ አያያዝና ስንፍናን ሊሆን ይችላል ።

" አትፍረዱ ይፈረድባችኋል" የሚለውን ቃል ለማስተዋል የተሳናቸውአንዳንድ ሰዎች በመሰል ወንድማቸውላይ ያልሠራውን ወንጀል ሠርተዋል እያሉ በከባድ ፍርድ ለማስገባት የሚሞክሩ እንዳሉ የታወቀ ነውየነገሩ አመጣጥና ቅንብር ከሥር መሠረቱ መርምረው በንጽሑ ሰው ላይ በሐሰት የተተበተበውን ክስ በቀላሉ ፈትተው እንደገና በተብታቢው ሰው ላይ ይጥሉታል/። ስለዚህ ነው አባቶች" ዳኛ የሚፈርደው ፡እርጉዝ የምትወልደው አይታወቅምና" ዳኛ ይገላግላችሁ እያሉ በሽምግልና መፍታት ያቃታቸውን ነገር አሳልፈው የሚሰጡት ።

ታሪክ እንደሚነግረን በድሮ ጊዜ ትክክለኛ ፍርድ የሚፈርዱ እንደነበሩ እንረዳለን ፡ በአንጻሩም ራሳቸው ደግሞ ለፍርድ የሚቀርቡበት ሰዓት እንዳለ ካለማወቃቸውም በላይ ከላይ የተሰጣቸውን ሥልጣን መከታ በማድረግ ያለ እንዳች አስተያየት በዘፈቀደ /በጭፍን/ እየፈረዱ ንጹሑን ሰው እስር ቤት ይከቱ እንደነበሩ እናነባለን ።

በእውነተኞች ፈራጆች የጠቢቡ ሰሎሞን ትክክለኛ ፍርድ ሲወሳ ይኖራል ፤ ለብዙ አስተያየትም መመሪያና የዕውቀታቸው ማዳበሪያ ሆኖላቸዋል ። ሰሎሞን በወጣትነቱ ዘመን አባቱ ዳዊት ተለየበት ሥልጣኑን ጨብጦ የእስራኤልን ሕዝብ በቅንነት ይመራ ነበር ።

ሥራውን በሚጀምርበትጊዜምአስቸጋሪ ፍርድ ገጥሞታል ። ይኸውም ሁለት ሴተኛ አዳሪዎች /ጋለሞቶች/ በአንድ ቤት ደባልሆነውየሚኖሩነበሩ ፡ እነዚህ ሴቶች ሁለቱም ወንዶች ልጆች ወልደው ሲኖሩ ሳለ እንዷ ሌሊት ተኝታ በዕንቅልፍልቧ ስትገለባጥልጅዋን አፍና ገደለችው ትንሽ ቆይታ ልታጠባው ብትቀሰቅሰው ሙቶ አገኘችው ወዲያውኑ ሬሣውን አንሥታ እንቅልፍበያዛትጓደኛዋክንድላይ አጋድማ ጤነኛውን የጓደኛዋን ልጅ ወስዳ ይዛ ተኛች ።

ያችም ከእንቅልፏ ነቅታ ልጅዋን ልታጠባ ብትዳብስ ሬሳ መታቀፏን ተረዳች ሬሣውም ልጅዋ እንዳልሆነ አወቀችና ከጓደኛዋ ጋር ያለው ልጅየራስዋመሆኑንተረድታ እንድትመልስላት በትሕትና ጠየቀቻት እርሷ ግን የኔልጅ ነው አንጂ ያንቺ አይደለም ብላ አልመልስም አለች ።

ሌሊቱ ሲነጋ ተያይዘው ወደ ዳኛ ሄዱ " ይህ አስደናቂ ዜና በመላዋ ኢየሩሳሌም ከመወራቱም በላይ ነገሩ በምን ዓይነት ሁኔታ ሊፈታ እንደሚቻል ለብዙዎቹ አስቸጋሪ ሆኖ ተገምቶ ነበር ። ጉዳዩ ወደ ወጣቱ ንጉሥ ሰሎሞን ደረሰና ሁለቱንም አቅርቦ በሰላም ለመፍታት ቢሞክር የማይሳካ ሆኖ አገኘው ። ነገር ግን ወጣቱ ሥራ ከመጀመሩ በፊት ከፈጣሪው የለመነው ልመና" ስለዚህ በሕዝብ ላይ መፍረድ ይችል ዘንድ መልካሙንና ክፋውንም ይለይ ዘንድ ለባሪያህ አስተዋይ ልቡና ስጠው አለዚያማበዚህ በታላቅ ሕዝብ ላይ ይፈርድ ዘንድ ማን ይችላል የሚል ስለነበረ እግዚአብሔር ለጠቢቡ ልዩ ማስተዋል ሰጠው።ይኸውምሁለቱን ሴቶች እፊቱአቅርቦ ሠይፍ አምጡልኝ አለ ፡ ሠይፍም አመጡለት ደህናውን ልጅ እኩል በኩል ከፈሉና ለሁለቱም ስጡአቸው አለ ። በዚሁ ወቅት እውነተኛ እናቱ ጌታዬ ሆይ! አይሆንም ለእርሷ ስጧት አለች ያች ግን ባልወለደ አንጀትዋ እኩል በኩል ይከፈልና ይሰጠን አለች ።

ጠቢቡ ሰሎሞን ሕፃኑ በቀላሉ የማን እንደሆነ ለማወቅ ቻለ ሕፃኑን ከአመጸኛዋ ሴት ወስዳችሁ በትክክል እናቱ ለሆነችው ሴት አስረክቧት አለ ።እንዲህ ያለው አስደናቂ ፍርድ በእስራኤል ሕዝብ ሁሉ በመሰማቱ በፊት በሰሎሞን ላይ !!ነበረው አስተያየት ይልቅ ጠለቅ ባለው ሁኔታ ተመለከተው ።

( ፩ኛ/ ነገሥት ፫፡፲፮ ።፳፰)

ከላይ እንደጠቀስነው ሳይመረምሩና ሳያጣሩ ፍርድ ከሰጡ ዳኞች መካከል ደግሞ ለማስረጃ ያህል ከዚህ እንደሚከ



www.ethiopianorthodox.org

ተለው እንጠቅሳለን አንድ ወጣት በአ ንድ ባለሥልጣን ቤት በአሽከርነት ሲ ሠራ የዳኛው ሚስት በወጣቱ ላይ አይ ንዋ አረፈ እጅግም ወደደችውና ከእር ስዋ ጋር እንዲተኛ ጠየቀችው ።

ቤት ጨመረው ፣ ወጣቱ ዮሴፍ ነው ፣ ዳኛው ወይም ባለሥልጣኑ ደግሞ የፈ ርኦን ቢትወደድ የነበረው ጲጥፋራ የ ሚባል ነው(ዘፍጥ ፴፱፥፪)

ከዚህ በላይ ያነበብነው ስለምድራው የማያዳግም የመጨረሻ ፍርድ ለእያንዳ ንዱ እንደሥራው ለማስረከብ ነው ።

ፍርዱ ምን እንደሚመስል ወንጌላ ዊው ዮሐንስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶ ስ የሚናገረውን እየተከታተለ ከመዘገ



የክርስቶስ ሁለተኛ መምጣት

ወጣቱ ግን አይሆንም በጌታዬ ሚስ ት እንዲህ ያለ ሥራ አልፈጽምም አላት ሴቲቱም የወጣቱን ቁርጥ ሀሳብ ከተረ ዳች በኋላ በግድ ለመያዝ ስትሞክር ቀ ሚሷ ከበስተፊቷ ተቀደደ እርሱምሮጡ አመለጣት ። ነገር ግን ሴትየዋ በነገሩ እጅግ ተናደደች ባልዋ ሲመጣ ይህ አሽ ከርህ እጅግ ጠግቦአል ልድፈርሽ ብሎ ሊይዘኝ ሲመጣ አልያዝም ብዬ ስሮጥ ቀሚሴን ቀደደው አለችው ባል ዋም ሥልጣኑን መከታበማድረግከእ ግዚአብሔር ና ከመንግሥቱ የተሰጠው ንም ኃላፊነት በማቃለል ወጣቱ ባልሠ ራው ሥራ እንደሠራ በመቁጠር እስር

ያን ሰዎች አመለካከትና ስለዳኞቻቸው ም ፍትሕና ርትዕ አሰጣጥ የሚመለከት ሐተታ ነው ፤በርእስ ትምርህቱ"ለፍ ርድ ትቀርባለህና ተዘጋጅ በሚል መነ ሻ ለመግቢያና ለማገናዘቢያ ያህል ገለ ጽን እንጂ የትምህርቱ ወርቃዊ ምሥ ጢር ግን ስለሰማያዊና ምድራዊ ንጉሥ ስለክርስቶስ ዳግም ምጽአት የሚያትት ነው ።

የክርስቶስ ደግሞ መምጣት ሥጋው ያን ዳኞች አንድን ነገር ግምትና አስተ ያየት ሰጥተውና አሻሽለው እንደሚፈ ርዱት ዓይነት ለመፍረድ ሳይሆን በመ ለኮታዊ ሥልጣኑ ወስኖ ያስቀመጠው

በው ቅዱስ ወንጌል ውስጥ "ዓለም በል ጁእንዲድንነውእንጂበዓለምእንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውም ና በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም ፣በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታ ል ብርሃንም ወደ ዓለም መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለወደዱ ፍርዱ ይህ ነው " የሚል ስለሆነ ከጨለማ ወጥተን በብ ርሃን ለመኖርየምንችልበትንመንገድ ይጠቁመናል ።(ዮሐ ፫፥፲፮-፲፱)

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ



ክርስቲያን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየ ሱስክርስቶስለእያንዳንዱሰው ዋጋውን ለማስረከብ ዳግመኛ ለፍርድ እንደሚ መጣ በየጊዜው ከማስተማርዋም በላይ ምንምእንኳያችንየሚመጣባትንሰዓት ማንም አያውቃትም ብሎ ራሱ ጌታችን ኢየሱስክርስቶስቢወስናት፳ኛ/በጳጉሜ ን ፪ኛ/ በደብረ ዘይት ምጽአት እንደሚ ፈጸም ታስተምራለች ይልቁንም በወር ኃ ክረምቱ ማለት ጳጉሜን ከመግባቱ በፊት ባሉት የነሐሴ ወር መጨረሻ ቀና ት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በኃጢአቱ እንዲናዘዝ ንስሐ እንዲገባና እንዲዘጋ ጅ ቤ/ክርስቲያን አጥብቃ ትመክራለች

ያም ሆነ ይህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስ ቶስ ተመልሶ ለፍርድ እንደሚመጣ ካ መን ነገ ከነገ ወዲያ ሳንል ንስሐ መግ ባት እንደሚገባን ሲያስጠነቅቀን እው ነት እላችኋለሁ ቃሌን የሚሰማ የላከኝ ንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለ ው ከሞትም ወደሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም" ብሎአል ።ከ ዚህም አያይዞ"እውነት እውነት እላች ኋለሁሙታንየእግዚአብሔርንልጅ ድ ምፅ የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል እር ሱም አሁን ነው" በማለት የተናገረው ቃል እጅግ አሳሳቢ ነው ይህ አምላካዊ ቃልየተወሰነቀንንንናወርንሰዓትንናደ ቂቃን ስለማያመለክት ዛሬውኑ ንስሐ መግባትና በጾምና በጸሎት መዘጋጀት ም እንደሚገባን ያስጠነቅቀናል ።

ከክርስቶስ ልደት በፊት የነበሩት ደ ጋግ አባቶች ይህ ምሥጢር አስቀድሞ ተከስቶላቸው ሲናገሩ እኔ ግን የሚበኸ ሕያው እንደሆነ በመጨረሻም ዘመን በምድር ላይ እንዲቆም ይህ ቁርበቴም ከጠፋ በኋላ በዚያን ጊዜ ከሥጋዬ ተለ ይቼ እግዚአብሔርን እንዳይ አውቃለ ሁ ብለው ለመናገር በቅተዋል( ኢዮብ በ፲፱፥፳፭-፳፯)

በተጨማሪም አሕዛብ በልዩ ልዩ ቋንቋም የሚናገሩ ሁሉ ይገዙለት ዘንድ ግዛትና ክብር መንግሥትም ተሰጠው ግዛቱም የማያልፍ የዘለዓለም ግዛት ነው መንግሥቱም ለዘላለም የማይጠፋ ነውብለው የመሠከሩትንምእናስታው ሳለን (ዳንኤ ፯፥፲)

እነዚህ ሁለት አባቶች ከክርስቶስ ልደት በፊት ብዙ ዘመናት ያሳለፉ ሲሆ ኑ ምንም እንኳ በሥጋ ሞት እንደሚጋ ረፉ ቢአውቁም ዘለዓለማዊ ሕይወት የሚሰጣቸው ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ መከራን እንደ ሚቀበ ልና እንደሚቀበር በሦስተኛው ቀን እን ደሚነሣ ከዚያም በኋል ወደ ስማይ እን ደሚያርግ ዳግመኛም ለፍርድ እንደሚ መለስ ተገልጾ ስለታያቸው ትንቢታቸ ውን በጽሑፍ መዝግበው አስተላ ልፈዋል ።

አዎን ክርስቶስ ለመጨረሻ ፍርድ ተመልሶ ወደዚህ ዓለም እንደሚመጣ ቅዱሳትመጻሕፍትተባብረውበታል በ ቅዱስ ወንጌል በየጊዜው ይታወጃል "የሰው ልጅ ከመላእክት ጋር በአባቱ ክብር ይመጣ ዘንድ አለውና ያንጊዜ ም ለሁሉ እንደሥራው ያስረክበዋል ይላል (ማቴ ፲፮፥፳፯) እናንተ የአባቴ ብሩካን ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የተዘጋጀላችሁን መንግሥት ውረሱ (ማቲ ፳፭፥፴፬) በማለት የመጨረሻ ፍ ርድ ሰጥቶ ያሰናብታቸዋል(ማቴ ፳፭ ፥ -፵፩) የሰው ልጅ መላእክቱን ይልካል ከመንግሥቱም እንቅፋትን ሁሉ ዓመ ጻንም የሚያደርጉትን ይለቅማሉ ወደ እቶን እሳትም ይጥሉአቸዋል በዚያ ልቅ ሶና ጥርስ ማፋጨት ይሆናል ጻድቃን ግንበአባታቸውመንግሥት እንደፀሐ ይ ይበራሉ(ማቴ ፲፫፥፵፩-፵፫)

አንባቢ ሆይ በእግዚአብሔር መንግ ሥት ገብተህ እንደፀሐይ እያበራህ ለመ ኖር ትችል ዘንድ በክርስቶስና ሕይወት ውስጥ ገብተህ በትክክል ትመራለህና ተንኰል ፣ ምቀኝነት ፣ክፋት ከንቱአም ልኮት የኃጢአት ተግባር የሆነውን ሁሉ እንደ አሮጌ ጨርቅ ከሰውነትህ አውል ቀህ ጥለኸዋልን? ሐዋርያው ቅዱስ ጳ ውሎስ አሮጌውን ልብስ አስወግዳችሁ አዲሱን ልብስ ክርስቶስን ልበሱ ብሎ አልና ።

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እነሆ የፍርድ ቀን ሳይመጣ ንስሐ ግባ እንግ ዲያስ ባትነቃ እንደሌባ እመጣብሃለሁ በማናቸውም ሰዓት እንድመጣብህ ከቶ አታውቅም ብሎአልና በመጨረሻ ፍር ድ መቅረብህ ስለማይቀር ክርስቶስን ንስሐ ገብተህ በሥጋው ወደሙ ተወ ስነህ ዋጋህን ለመቀበል ተዘጋጅተህ ጠ ብቀው ።

ገብረ ክርስቶስ ኃይለ ማርያም

---

# የግብርና በረከት

ከገጽ ፮ የዞረ

ረ. የዕጽዋት እንክብካቤ እጽዋቱ ከተ ዘራና መብቀል ሲጀምር በእጅ ማረ ም ቀጥሎም መኮትኮት እንዲሁም ብዙ እድገት በአንድ ቦታ ላይ ከመ ጠን በላይ ከተገኘ ማሳሳት ተገቢ ነው ።

ሰ. የመመገቢያ ወቅት ፣ የከብት ድን ችን በቀላሉ ከመሬት ላይ በመንቀል አፈሩን ከሥሩ ላይ ጠረግ ጠረግ በማድ ረግና ከዚያም በመከታተፍ መመ ገብ ይቻላል ። ይኸም ዘዴ ከጥቅምት እስከ በልግ ወራት ቢካሄድ የተሻለ ነው ። በአርሲ ገጠር ልማት ድርጅት በተገኘው የአመጋገብ ውጤት መሠ ረት ለአንድ ላም ከ፰ - ፲፪ ኪሎ የከ ብት ድንች መመገብ እንደሚቻል ተደርሶበታል ። በመጨረሻም እንደ የከብት ድንች ከፍተኛ ምርትን ባይ ሰጡም ከሥራ ሥር ቤተሰቦች እንደ ነታርኒፕ ፣ ስናድ ፣ የሸገር ቢሐና የስኳር ድንችን የመሳሰሉ ለመኖነት በጥናት መሞከራቸውን እናስታው ቃለን ።

በለጠ አበበ



www.ethiopianorthodox.org

# ዘመን ካልሠሩበት

ከገጽ ፭ የዞረ

ጥ ነው ። ይህ ደግሞ የሚገሥጸኝ ዲዮጋንስ ነው ሌላውም በጎ በጎውን ነገር በመናገር ተስፋ የሚሰጠኝና የሚያጽናናኝ ሶቅራጥስ ነው ። በጐ በጐውን እየመጣ የሚያጫውተኝ አፍላጦን ነው ።

በዚሁ አንፃር አርስጣጣሊስ ይመሰክራል ሕርሙስ ይጨወታል ዳዊት ይዘምራል ሰሎሞን ይገሥጻል ሲራክ ይመክራል ባስልዮስ ያስተምራል ጎርጎርዮስ ይናገራል ሐዋርያ ይሰብካል ወንጌል ያበሥራል ከነዚህ ሁሉ ከፈቀድኩት ጋር እነጋገራለሁ እወያያለሁ የተዘነጋኝን ሁሉ ያስተውሱኛል ስለዚህ ብቻዬንና ሥራ ፈት ሆኜ ዘመኔን በከንቱ እንዳሳለፍኩ አልቆጥረውም ብሎ እንደመለሰለት ተጽፎ ይገኛል ።

በተለይ ይህ የሚያስተምረን ሁሉ በተሠማራበት የሥራ መስክ ከተሰማራ ዘመኑን በከንቱ እንዳላሣለፈ ነው ።

ለምሳሌ በገበሬዎች ብዙ ምርት ከአመረቱ ነጋዴዎች ተገቢ ትርፍ ከአስገኙ አስተማሪዎች በትጋት ከአስተማሩ ተማሪዎች ፈተናቸውን ከአለፉ የወንጌል መምህራን በእውነት የእግዚአብሔርን ቃል ከመሰከሩ በዘመኑ ሠሩበት እንጂ እንደሠራባቸው አይቆጠርም ምክንያቱ ለእያንዳንዱ የተለየ ሰጦታ አለውና ነው ።

እንዲያውም አዲስ ዘመን የምንለው በሀገራችን የዘመን መለወጫ ወቅት የክረምቱ ወቅት እየተገባደደ ምድሪቱ ለምልማና አብባ የምትታይበት ጊዜ በመሆኑ ቀደም ካሉት ወራት የተለየ እናደርገዋለን ።

ከዚህም ሌላ በክረምቱ ምክንያት ተለያይተው የነበሩት ዘመድ አዝማድ የሚገናኙበት ስለሆኑ እንጂ የሁሉም የሥራ ውጤት የሚገመገመው የዘመን መለወጫ ከመድረሱ ከሁለት ወራት በፊትመሆኑን ሁላችንም እናውቃለን።

ይሁን እንጂ ወራቶቹን የሚያጠቃልለው የዘመን መለወጫ ስለሆነ የአዲስ ሥራ መጀመሪያ አድርገን መቁጠርና ያለፈውን ዘመን ምን ሠራሁበት ብሎ ማሰብ ያስፈልጋል ።

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለራሱ የኑሮ ትርጉም ሲያትት "እኔ ከቶ በሕይወት ብኖርም ባልኖርም በምንም ነገር አላፍርም ለእኔ ምንም ቢሆን ሕይወት ሁሉም ጥቅሜ ነውና ካለ በኋላ ነገር ግን በሥጋ መኖር ለእኔ ፍሬዬ ስለሆነ ከእነዚህ ከሁለቱ የምመርጠውን አጣለሁ ሆኖም ስለ ክርስቶስ ለመናገር በሥጋ መኖርን እመርጣለሁ ። " ብሏል ። ፊልጵ. ፩. ቁ. ፳

ሐዋርያው ብኖርም ባልኖርም ካድየለኝም ሲል የተናገረው መልካም ተግባር ስላለው ነው ። መልካም ተግባር እንደዚህ ያስመካል እንደልብም ያናግራል ። ስለዚህ እኛም እንደልባችን ለመመካት እንድንችል በየዕለቱና በየሰዓቱ በየዓመቱም የምንሠራው ሥራ ለሰማያዊ ኑሮአችን ጭምር ዋስትና ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል ።

ዕድሜ ምንም እንኳን ሕይወት ላለው ፍጡር የማይሠለች ምግብ ቢሆንም በተለይ ሰው ዓመታትንና ዘመናትን እንደልብስ እየቀያየሩ ፣ ብዛቱንም እየለኩና ጊዜውን ለማራዘም ያለው ጥረት ቀላል አይደለም ። እርግጥ ነው ለሰው ሰፊ ወራትና ረጅም ዘመናት ያስፈልገዋል ።

ይሁን እንጂ ሰው ረጅም ዕድሜና ጤና የሚመኘው ያለፈውን ስሕተቱን ለማረምና በረጅም ጊዜ ውስጥ ብዙ ተግባር ፈጽሞ መልካም ውጤትን ለማግኘት እንጂ ዕድሜን እየቆጠሩና እየሠሩ ይህን ያህል ዘመን አለኝ ለማለት ለጉራ ወይም ተቋርጦ የቀረውን የኃጢአት ቅሬታ ለማስተካከል ። መሆን የለበትም ።

እንግዲህ በአንዳንድ ክፍላተ ዓለም ያሉ ሕዝቦች አዋቂዎችና ብልሆች የሆኑት የዘመንን ጉዞ ተከትለው ተባብረው ስለሠሩና የጊዜንም ጠቃሚነት ስለአወቁ ነው ። ይህን ባይረዱ ኑሮ የዘመኑ ጠበብት ተብለው ባልተጠሩና ባልታወቁ ነበር ።

ስለዚህ ዘመን ያልፋል ዘመን ያረጃል ሥራ ግን የማያረጅ ሁልጊዜ አዲስ ስለሆነ ባለፈው ዓመት ያልሠራን እንድንሠራ የሠራን በሥራችን እንድንደሰት ያስፈልጋል ምክንያቱም ዘመን ካልሠሩበት ቢቆጥሩት አይጠቅምም ተብሎ ተጽፎአልና ።

ሊቀ ልሳናት ነቅዓ ጥበብ ወንድም

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፩ የዞረ

በተጨማሪም በአሳብም በጉልበትም መርዳት ነው ።

ይህንን ያደረጋችሁ እንደሆነ አንተና ጓደኞችህ የቤተ ክርስቲያን አፍቃሪዎች አክባሪዎች ለመባል ትችላላችሁ ።



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፤ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፤ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቁ. 116616
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org